# የወላጆችና የልጆች ልዩ የትምህርት መብቶች

ልጅዎ በአሁኑ ሰዓት ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን እያገኘ/ች ካልሆነ/ች ይህ አነስተኛ የማስታወቂያ ጽሁፍ (ብሮሸር) የተሰጠዎት ልጅዎ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን እንዲያገኝ/እንድታገኝ እርስዎ ስለጠየቁ ወይም እኛ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች አስፈላጊ ናቸው ብለን ስለምናምን ነው። የጋራ ዓላማችን ዕድሉ ካለ ልጅዎ የሚያስፈልገውን/የሚያስፈልጋትን ለሕዝብ ሁሉ ተደራሽ መሆን ያለበትን ነጻና ተገቢ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም ("FAPE") ማግኘቱን/ቷን ማረጋገጥ ነው። ይህንን ዓላማ እውን ለማድረግ ልጅዎ የትኛው ዓይነት ጉድለት (ውስንነት) እንዳለበት/እንዳለባት ለማወቅና ካለበትም/ካለባትም ለልጅዎ የትኛው ዓይነት ልዩ የትምህርት ፕሮግራምና አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉ ለመወሰን ልጅዎን መገምገም ("መፈተን") እንፈልጋለን። እነዚህ ፈተናዎች ለልጅዎ ብቻ የተመረጡ ቁሳቁሶችንና የአሰራር ሂደቶችን የሚጠቀሙ ሲሆን መሰረታዊ ፈተናዎችን ወይም በክፍል ውስጥ፣ በክፍል ደረጃ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ለሁሉም ተማሪዎች በተለምዶ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችንና የአሰራሪ ሂደቶችን አያካትቱም። ይህ ግምገማ (ምዘና) የሚደረገው የፌዴራልንና የአገርን መስፈርቶች በጥብቅ በመከተል ይሆናል። ግምገማውን (ምዘናውን) ተከትሎ ሙሉ ውጤቶችን የምንሰጥዎ ሲሆን ልጅዎ ልዩ ትምህርትንና ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን በሚሰበሰበው ቡድን እንዲሳተፉ እንጋብዝዎታለን፡ ልጅዎ ብቁ ሆኖ ከተገኘ ለልጅዎ በግል የሚዘጋጀውን የትምህርት ፕሮግራም ("IEP") እንድንቀርጽና ከልጅዎ ፍላጎቶች ጋር የተገናኙ ድጋፍ ሰጭ አገልግሎቶችን ለመለየት እንዲረዱን እንጠይቅዎታለን። እርስዎ ከፈለጉ ለልጅዎ በግል የሚዘጋጀውን የትምህርት ፕሮግራም ("IEP") በሚቀርጸው በዚህ ስብሰባ ላይ ሌሎች ሰዎችም እንዲገኙ መጠየቅ ይችላሉ።

ልጅዎ አስቀድሞ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን በማግኘት ላይ ካለ ይህ አነስተኛ የማስታወቂያ ጽሁፍ እየተሰጠ ያለበት ምክንያት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ይህንን እንድናደርግ ስለምንጠየቅ፣ በዚህ የትምህርት ዓመት እርስዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ጉዳይዎ ተገቢ በሆነ የህግ አግባብ እንዲታይልዎ ስለጠየቁ ወይም ከመንግሥት የቅሬታ ምርመራ የተነሣ፣ የእርምት እርምጃ አወሳሰድ ላይ ለውጥ ለማድረግ ሀሳብ እያቀረብን ስለሆነ ወይም እርስዎ ቅጂው እንዲሰጥዎ ስለጠየቁ ሊሆን ይችላል።

ይህ ሂደት የእርስዎን ንቁ ተሳትፎና ትብብር ይሻል። **ልጅዎን ከእርስዎ የበለጠ በተሻለ ሁኔታ የመረዳት ዕድል ያለው ሌላ ማንም የለም።** ሕግም እርስዎ የሚሰጡአቸው ሀሳቦች መካተታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዱ ዘዴዎችን ያስቀምጣል። ከዚህ በተጨማሪ እኛ ያቀረብናቸውን ሀሳቦች ወይም መቀበል እምቢ ያልናቸውን ነገሮች ለመቃወም እና የሚፈጠሩ ቅሬታዎችን (አለመስማማቶችን) ለየትኛውም ወገን ሳያዳላ የሚፈታ (ገለልተኛ) ግለሰብ እንዲመደብ ሕጉ መንገዶችን ያስቀምጣል። የፌዴራልና የመንግሥት ልዩ የትምህርት ሕጎች የሚሰጡአቸው የእነዚህ ሰፊና ውስብስብ የሆኑ መብቶች ስብስብ በጥቅሉ "የወላጆችንና ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸውን ልጆች መብቶች የሚጠብቁ የአሰራር ሂደቶች" ተብለው ይጠራሉ። የዚህ አነስተኛ የማስታወቂያ ጽሁፍ ዓላማ ለእነዚህ መብቶች አጭር መግለጫ መስጠት ነው። የዚህ ሙሉ መግለጫ ትምህርት ቤትዎ በሚገኝበት የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ወይም ኔቫዳ የትምህርት ክፍል ይገኛል።

## *ተጨማሪ እርዳታ ከየት ማግኘት እንደሚቻል*

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ተጨማሪ ዕርዳታና መረጃ የሚያገኙበት የመጀመሪያ ቦታ ነው። ከልጅዎ መምህር ወይም ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ጋር፣ ትምህርት ቤትዎ በሚገኝበት የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል የልዩ ፍላጎት ሥራ መሪ ጋር ወይም የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ተቆጣጣሪ ጋር መነጋገር አለብዎት። ደግሞም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቢሮ ማነጋገር ይችላሉ፡-

Nevada Department of Education Office of Inclusive Education
700 East Fifth Street, Suite 106 Carson City, Nevada 89701-5096

(775) 687-9171 ወይም በነጻ ስልክ፣ 1-800-992-0900፤ የውስጥ መስመር፣ 79171

ይህ ሰነድ በኤሌክትሮኒካዊ ዘዴ በሚከተለው ስፍራ ይገኛል፣
https://doe.nv.gov/Inclusive_Education/IDEA_Forms__Documents/

## *አስቀድሞ በጽሁፍ የሚሰጥ ማሳሰቢያ/ማስታወቂያ*

### ማሳሰቢያ

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል በሚከተሉት ምክንያቶች የጽሁፍ ማሳሰቢያ (አንዳንድ መረጃዎችን በጽሁፍ) ሊሰጥዎ ይገባል፡-

1. ለልጅዎ መታወቂያን፣ የምዘና ወይም የትምህርት ምደባን ለማስተዋወቅ ወይም ለውጥ ለማድረግ፣ ወይም ለሁሉም ተደራሽና ተገቢ የሆነ ነጻ ትምህርት ለማቅረብ ሀሳብ ሲያቀርብ፤ **ወይም**
2. ለልጅዎ መታወቂያን፣ የምዘና ወይም የትምህርት ምደባን ለማስተዋወቅ ወይም ለውጥ ለማድረግ፣ ወይም ለሁሉም ተደራሽና ተገቢ የሆነ ነጻ ትምህርት ማቅረብን እምቢ ስል

### የማሳሰቢያው ይዘት

የጽሁፍ ማሳሰቢያው የሚከተሉትን ነገሮች ማካተት አለበት፡-

1. የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል እርምጃ ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ የሚያቀርበውን ሀሳብ መግለጽ አለበት፤
2. የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል የድርጊቱን ሀሳብ ለማቅረብ ወይም ላለማቅረብ ሲወስን የተጠቀመበትን እያንዳንዱን የምዘና ቅደም ተከተልን፣ ዳሰሳን እና መረጃን መዝግቦ የያዘበትን ዘገባ መግለጽ አለበት፤
3. ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል "ለ" ውስጥ የአሰራር ቅደም ተከተል መጠበቂያዎች በሚል ርዕስ ሥር ከለላዎች እንዳሉዎ የሚገልጸውን አረፍተ ነገር ማካተት አለበት፤
4. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል ለመተግበር ወይም ላለመተግበር እያቀረበ ያለው ሀሳብ ለምዘናው የመነሻ ማጣቀሻ ካልሆነ የወላጆችንና ጉድለ!ት (ውስንነት) ያለባቸውን ልጆች መብቶች የሚጠብቁ የአሰራር ሂደቶችን መግለጫ (የሰነዱን ቅጂ) እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መንገር አለበት፤
5. ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) አካል የሆነውን ክፍል "ለ"ን መረዳት እንዲችሉ የሚረዱ መረጃዎችን ማካተት አለበት፤
6. ለልጅዎ በግል ደረጃ የሚዘጋጅ የትምህርት ፕሮግራምን (IEP) ያዘጋጀው ኮሚቴ ከግምት ውስጥ ያስገባቸውን ሌሎች ምርጫዎችንና እነዚያ ምርጫዎች ተቀባይነት ያጡባቸውን ምክንያቶች መግለጽ አለበት። **እናም**
7. የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ድርጊቱን ለመተግበር ወይም ላለመተግባር የወሰነባቸውን ሌሎች ምክንያቶችን መግለጫ መስጠት አለበት።

### ማሳሳቢያው/ማስታወቂያው ሊስተዋል በሚችል ቋንቋ

ማሳሰቢያው፡-

1. አጠቃላይ ሕዝብ ሊያስተውለው በሚችል ቋንቋ መጻፍ አለበት።

2. ግልጽ በሆነ ምክንያት ማድረግ ካልተቻለ በቀር በአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም እርስዎ በሚጠቀሙአቸው ሌሎች የተግባቦት መንገዶች መሰጠት አለበት።

የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም ሌሎች የተግባቦት መንገዶችዎ በጽሁፍ የማይገለጹ ከሆኑ፡-

1. ማስታወቂያው በቃል ወይም በአገርዎ ቋንቋ በሌሎች መንገዶች ወይም በሌሎች የተግባቦት መንገዶች ይተረጎምልዎታል። ወይም ፤
2. የማስታወቂያውን ይዘት እንዲረዱ ይደረጋል፤ እና
3. በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተጻፉ ነገሮች ተፈጻሚ ስለመሆናቸው የጽሁፍ ማስረጃ ይኖረል።

## *አፍ መፍቻ ቋንቋ*

የእንግዚዝኛ ቋንቋን የመረዳት ውስንነት ካለበት ሰው አንጻር ጥቅም ላይ ሲውል ***የአፍ መፍቻ ቋንቋ*** ማለት የሚከተሉትን ማለት ነው፡-

1. በተለምዶ ያ ግለሰብ የሚጠቀመው ቋንቋ ወይም ልጅን በተመለከተ ወላጆቹ የሚጠቀሙት ቋንቋ ማለት ነው።
2. ከልጁ ጋር በሚደረጉ ቀጥተኛ ግንኙነቶች በሙሉ (ልጁን መገምገምን ጨምሮ) ጥቅም ላይ የሚውለው ቋንቋ ልጁ በተለምዶ በቤቱ የሚጠቀመው ወይም በትምህርት ቤት አከባቢ የሚጠቀመው ቋንቋ ማለት ነው።

መስማት ወይም ማየት ለተሳነው ሰው ወይም የጽሁፍ ቋንቋ ለሌለው ሰው የተግባቦት ዘዴ ሊሆን የሚችለው ግለሰቡ በተለምዶ የሚጠቀምበት ነገር (የምልክት ቋንቋ፣ የዓይነ-ሥውራን ማንበቢያ ጽሁፍ/ብሬይል ወይም የቃል ግንኙነት) ነው።

## *በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚላክ ደብዳቤ*

የወረዳዎ ትምህርት ቢሮ ወላጆች ሰነዶችን በኢሜይል እንዲቀበሉ ምርጫን ከሰጠ የሚከተሉትን ሰነዶች በኢሜይል ለመቀበል መምረጥ ይችላሉ፡-

1. ቅድሚያ የጽሁፍ ማሳሰቢያን፤
2. የአሰራር ቅደም ተከተል መጠበቂያዎችን ማሳሰቢያ፣ እና
3. ከአሰራር ሂደት ጋር የተገናኝ ቅሬታን የሚመለከቱ ማሳሰቢያዎችን

## *የወላጅ ስምምነት*

### ስምምነት

*ስምምነት ማለት፡-*

1. እየተስማሙበት ስላለው ተግባር ስለሚያስፈልግዎት መረጃ በሙሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌሎች የተግባቦት ዘዴዎች (የምልክት ቋንቋ፣ ብሬይል ወይም የቃል ግንኙነት) የተሟላ መረጃ አግኝተዋል ማለት ነው፤
2. ያንን ተግባር ተረድተው በጽሁፍ ይስማማሉ፣ ስምምነቱ ያንን ተግባር በመዘርዘር የሚለቀቀውን ዘገባና ለማን እንደሚለቀቅ ይመዘግባል ማለት ነው፤ **እናም**
3. ስምምነቱ በእርስዎ በኩል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተና በማንኛውም መንገድ ከስምምነቱ መውጣት እንደሚችሉ አስተውለዋል ማለት ነው።

ከስምምነት መውጣትዎ የስምምነት ቃል ከሰጡ በኋላ የተከሰተ ተግባርንና ከስምምነቱ ከመውጣትዎ በፊት የተከሰተ ተግባርን አያፈርስም (አይሰርዘውም)። በመጀመሪያ ለልጅዎ ልዩ ትምህርትና ከዚህ ጋር የተገናኙ አገልግሎቶች

ከተሰጡት/ጧት በኋላ ልጅዎ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን እንዲቀበል/እንድትቀበል የተስማሙበትን ስምምነት እርስዎ በጽሁፍ ከሰረዙ ስምምነቱን በመሰረዝዎ ምክንያት ልጅዎ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች መቀበሉን/ሏን የሚያሳዩ ማናቸውንም ማጣቀሻዎች ለማስወገድ የአከባቢ የትምህርት አስተዳደር ክፍል የልጅዎን የትምህርት ዘገባዎች ማሻሻል አይጠበቅበትም።

## የመነሻ/የመጀመሪያ ግምገማ (ምዘና) እንዲደረግ ስምምነት

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ለመተግበር የቀረበውን ሀሳብ በተመለከተ አስቀድሞ የጽሁፍ ማሳሰቢያን ሳይሰጥና ***የወላጅ ስምምነት*** በሚለው ርዕስ ሥር በተገለጸው መሰረት ስምምነትዎን ሳያገኝ ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል ለ ሥር ልጅዎ ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ለመቀበል ብቁ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የመነሻ ግምገማን (ምዘናን) ማድረግ አይችልም። የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ልጅዎ ጉድለት (ውስንነት) ያለበት መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ስለሚደረገው የመነሻ ግምገማ (ምዘና) ከእርስዎ በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነትን ለማግኘት ምክንያታዊ የሆነ ጥረት ማድረግ አለበት። የመነሻ ግምገማ (ምዘና) እንዲደረግ መስማማት ማለት የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ለልጅዎ ልዩ ትምህርትንና ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ማቅረብ እንዲጀምርም ተስማምተዋል ማለት አይደለም።

ልጅዎ በመንግሥት ትምህርት ቤት ተመዝግቦ ካለ ወይም በመንግሥት ትምህርት ቤት እንዲመዘገብ ፍላጎት እያሳዩ ግን ስምምነት ለመፈጸም እምቢ ካሉ ወይም የመነሻ ግምገማ ለማድረግ ለቀረበው ጥያቄ መልስ መስጠት ካልቻሉ የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር፣ እንዲያደርገው የሚጠበቅበት ባይሆንም፣ ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸውን ግለሰቦች የሚመለከተውን የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ሽምግልና፣ በጽሁፍ የሚቀርብ አቤቱታን፣ የውሳኔ ስብሰባን ወይም ያለው ልዩነት የሚፈታበትን ገለልተኛ የሆነ ህጋዊ ሂደትን በመጠቀም በልጅዎ ላይ የመነሻ ግምገማን (ምዘናን) ለማካሄድ ሊፈልግ ይችላል። የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የልጅዎን ግምገማ (ምዘና) ካላካሄደ ልጅዎን ቦታ ለማስያዝ፣ ለይቶ ለማወቅና ለመመዘን ያሉትን ግዴታዎቹን አይጥስም።

## በአንድ *የመንግሥት ዘርፍ ጥበቃ ሥር* ላለ/ላለች ልጅ የመነሻ ግምገማ (ምዘና) ለማድረግ የሚያገለግሉ ልዩ ደንቦች

አንድ ልጅ/አንዲት ልጅ ጉድለት (ውስንነት) እስካለበት/ባት ድረስ በአንድ የመንግሥት ዘርፍ ጥበቃ ሥር ከሆነ/ች እና ከወላጆቹ/ቿ ጋር እየኖረ/ች ካልሆነ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የመነሻ ግምገማን/ምዘናን ለማድረግ በሚከተሉት ሁኔታዎች የወላጅን ስምምነት አይሻም፡-

1. እንደዚህ ለማድረግ ምክንያታዊ ጥረቶች ቢደረጉም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የልጁን/የልጅቷን ወላጅ ማግኘት ካልቻለ፤
2. በአገሩ ሕግ መሰረት የወላጆች መብቶች ተቋርጠው ከሆነ፤ **ወይም**
3. ዳኛ የትምህርት ውሳኔዎችን እንዲያደርግና መነሻ ምዘና ለማድረግ ስምምነት እንዲፈጥር ወላጅ ላልሆነ ግለሰብ መብት ከሰጠ።

ጉድለጽ/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለው፣ በአንድ ***የመንግሥት ዘርፍ ጥበቃ ሥር ያለ ልጅ*** ማለት ልጁ በሚኖርበት አገር በተወሰነው መሰረት ልጁ፡-

1. የማደጎ ልጅ ነው።
2. በአገር ሕግ ሥር በአንድ *የመንግሥት ዘርፍ ጥበቃ ሥር* እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።
3. ልጁ ያለው በመንግሥት የልጅ ደህንነት ጥበቃ ወኪል አሳዳጊነት ውስጥ ነው።

በአንድ *የመንግሥት ዘርፍ ጥበቃ ሥር መሆን* የሚለው ሀሳብ አሳዳጊ ወላጅ ያለውን የማደጎ ልጅ አያካትትም።

## አገልግሎቶችን ለማግኘት የወላጅ ስምምነት

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ልዩ ትምህርትንና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ለልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመስጠቱ በፊት የእርስዎን በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነት ማማኘት አለበት። የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ልዩ ትምህርትንና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ለልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመስጠቱ በፊት የእርስዎን በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነት ለማግኘት ምክንያታዊ ጥረቶችን ማድረግ አለበት። ልጅዎ ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያገኝ መስማማትዎን እንዲያሳውቁ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ካልሰጡ ወይም የዚህን ዓይነት የስምምነት ሀሳብ መስጠት እምቢ ካሉ የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡-

1. ስምምነትን ወይም ያለ እርስዎ ስምምነት ልዩ ትምህርትና ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው አገልግሎቶች ለልጅዎ እንዲሰጡ የሚያደርገውን ውሳኔ ለማግኘት የወላጆችንና ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ልጆች መብቶች የሚጠብቁ የአሰራር ሂደቶችን (ይህ ማለት ሽምግልናን፣ አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብን፣ ውሳኔ ሰጪ ስብሰባን ወይም ገለልተኛ የሆነ የህግ ሂደትን) ላይጠቀም ይችላል።
2. ለልጅዎ ተጨማሪ አገልግሎቶችን መስጠት ባይችልም ለሁሉም ተደራሽ የሆነ ተገቢና ነጻ ትምህርትን (FAPE) እንዲያገኝ ማድረግ መስፈርቶችን መጣስ አይደለም።
3. ለልጅዎ ልዩ ትምህርት ለሚያስፈልገው ጉድለት/ውስንነት ላለበት ለእያንዳንዱ ልጅ የተዘጋጀ የትምህት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባን ወይም  ጉድለት/ውስንነት ላለበት ለእያንዳንዱ ልጅ በግል የሚዘጋጀውን የትምህርት ፕሮግራም ማዘጋጀት አያስፈልግም።

ልጅዎ ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልገሎቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ካገኘ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ልዩ ትምህርቱንና ተዛማጅነት ያላቸውነ አገልግሎቶች በቀጣይነት እንዳይሰጥ ስምምነትዎን ካቋረጡ  የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር፡-

1. ለልጅዎ ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልገሎቶች መስጠቱን ላይቀጥል ይችላል፣ነገር ግን አገልግሎቶቹን ከማቋረጡ በፊት ቅድሚያ የጽሁፍ ማሳሰቢያ መስጠት አለበት፤
2. ስምምነትን ወይም ያለ እርስዎ ስምምነት ልዩ ትምህርትና ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው አገልግሎቶች ለልጅዎ እንዲሰጡ የሚያደርገውን ውሳኔ ለማግኘት የወላጆችንና ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ልጆች መብቶች የሚጠብቁ የአሰራር ሂደቶችን (ይህ ማለት ሽምግልናን፣ አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብን፣ ውሳኔ ሰጪ ስብሰባን ወይም በመካከል ያለው ልዩነት የሚፈታበትን ገለልተኛ የሆነ ህጋዊ ሂደትን) ላይጠቀም ይችላል፤
3. ለልጅዎ ተጨማሪ አገልግሎቶችን መስጠት ላልቻለበት ለሁሉም ተደራሽ የሆነ ተገቢና ነጻ ትምህርትን (FAPE) እንዲያገኝ ማድረግ መስፈርቶችን መጣስ አይደለም፤ **እና**
4. ለልጅዎ ልዩ ትምህርት ለሚያስፈልገው ጉድለት/ውስንነት ላለበት ለእያንዳንዱ ልጅ የተዘጋጀ ልዩ የትምህት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባን ወይም  ጉድለት/ውስንነት ላለበት ለእያንዳንዱ ልጅ የሚዘጋጀውን ሕጋዊ የትምህርት ፕሮግራምን ማዘጋጀት አያስፈልግም።

## ለድጋሚ ግምገማዎች (ምዘናዎች) የወላጅ ስምምነት

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር የሚከተሉትን ነገሮች ማሳየት ካልቻለ በስተቀር ልጅዎን እንደገና ከመገምገሙ (ከመመዘኑ) በፊት የእርስዎን በመረዳት ላይ የተመሰረተ ስምምነት ማግኘት አለበት፡-

1. ልጅዎን እንደገና ለመገምገም (ለመመዘን) የእርስዎን በመረዳት ላይ የተመሰረት ስምምነት ለማግኘት ምክንያታዊ እርምጃዎችን መውሰዱን፤ **እና**
2. እርስዎ መልስ አለመስጠትዎን።

ልጅዎ እንደገና እንዲገመገም ካልተስማሙ የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር፣ እንዲያደርግ ባይጠበቅበትም፣ ልጅዎን እንደገና ለማስገምገም አለመስማማትዎን ባለመቀበል በሽምግልና፣ አቤቱታን በጽሁፍ በማቅረብ፣ ውሳኔ ሰጭ ስብሰባን በማድረግ ወይም ገለልተኛ የሆነ መደበኛ የህግ ሂደቶችን በመጠቀም የልጅዎን እንደገና መገምገም ሊከታተል ይችላል። በመነሻ ግምገማው እንደነበረው ሁሉ የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር በዚህ ሁኔታ እንደገና መገምገሙን ካልቀጠለ ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል ለ ሥር ያሉትን ግዴታዎቹን አይጥስም።

## የወላጅ ስምምነትን ለማግኘት የተደረጉ ምክንያታዊ ጥረቶችን መሰነድ

ትምህርት ቤትዎ ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ለመስጠት፣ እንደገና ለመገምገም፣ እና የመነሻ ግምገማዎችን ለማድረግ እና በመንግሥት የሕግ ጥበቃ ሥር ያለ ልጅ ወላጆች ያሉበትን ቦታ ለማመልከት የወላጅ ስምምነትን ለማግኘት የተደረጉ ምክንያታዊ ጥረቶችን ሰነድ መጠበቅ አለበት። ሰነዱ በእነዚህ አከባቢዎች ያደረጋቸውን ከዚህ በታች የተገለጹትን ጥረቶች ቋሚ መረጃ ማካተት አለበት፡-

1. የተደረጉ ወይም የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎችን ዝርዝር መረጃና የጥሪዎቹን ውጤቶች፤
2. ለወላጅ የተላኩ ደብዳቤዎችን ቅጂዎችና የተሰጡ መልሶችን፤ **እና**
3. ወደ ወላጅ ቤት ወይም ተቀጥረው ወደሚሰሩበት ቦታ የተደረጉ ጉብኝቶችን ዝርዝር መረጃዎችና የእነዚህ ጉብኝቶች ውጤቶች።

## ሌሎች ለስምምነት የሚያስፈልጉ ነገሮች

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር የሚከተሉትን ነገሮች ከማድረጉ በፊት የእርስዎን ስምምነት አይፈለግም፡-

1. የልጅዎ ግምገማ ወይም እንደገና ግምገማ አካል አድርጎ ያለውን መረጃ መከለስ
2. ከፈተናው ወይም ከግምገማው በፊት ከሁሉም ልጆች ወላጆች ስምምነት ካላስፈለገ በስተቀር፣ ለሁሉም ሌሎች ልጆች የተሰጠውን ፈተና ለልጅዎ መስጠት ወይም ሌላ ግምገማ ማድረግ።

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ለአንድ አገልግሎት ወይም ተግባር አለመስማማትዎን፣ ለልጅዎ ማንኛውንም ሌላ አገልግሎት፣ ጥቅም ወይም እንቅስቃሴ ለመንፈግ እንደ ምክንያት አይጠቀምም።

ልጅዎን በራስዎ ወጪ በግል ትምህርት ቤት አስመዝግበው ከሆነ ወይም ልጅዎን እቤት ውስጥ እያስተማሩ ከሆነ እና በልጅዎ ላይ የመነሻ ግምገማ ወይም ድጋሚ ግምገማ እንዲደረግ ካልተስማሙ፣ ወይም ስምምነትዎን እንዲገልጹ ለቀረበልዎ ጥያቄ መልስ ካልሰጡ፣ የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር የአሰራር ቅደም ተከተሎችን (ይህ ማለት ሽምግልናን፣ አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብን፣ ውሳኔ ሰጭ ስብሰባ ማድረግን ወይም ገለልተኛ የሆነ መደበኛ የህግ ሂደት መከተልን) ችላ ለማለት የራሱን መስማማት መጠቀም አይችልም። እንዲሁም ልጅዎ ፍትሃዊ አገልግሎቶችን (ወላጆች በግል ትምህርት ቤቶች ላስገቡአቸው ጉድለት/ውስንነት ላለባቸው ልጆች የሚሰጡ አገልግሎቶች) ለማግኘት ብቁ እንደሆነ ተደርጎ እንዲታሰብ አይጠበቅም።

# *ነጻ (ጥገኛ ያልሆኑ) የትምህርት ግምገማዎች/ምዘናዎች*

## አጠቃላይ

ከዚህ በታች እንደተገለጸው ስለ ልጅዎ ከአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል በተገኘው የግምገማ ውጤት ላይ ካልተስማሙ ስለ ልጅዎ ነጻ የሆነ የትምህርት ግምገማ (IEE) የማግኘት መብት አለዎት። ነጻ የሆነ የትምህርት ግምገማ እንዲደረግ ከጠየቁ የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ነጻ የሆነ የትምህርት ግምገማን ከየት ማግኘት እንደሚችሉ እና ነጻ ለሆኑ የትምህርት ግምገማዎች ጥቅም ላይ ስለሚውሉ የአከባቢው ትምህርት ቤቶች አስተዳደር መስፈርቶች መረጃ ሊሰጥዎ ይገባል።

## ትርጉሞች

ነጻ የትምህርት ግምገማ ማለት ለልጅዎ ትምህርት ሀላፊነት ባለበት በአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ተቀጣሪ ባልሆነ ብቃት ባለው ፈታኝ የሚደረግ ግምገማ ነው። የሕዝብ ወጪ ማለት የአከባቢው ትምህርት አስተዳደር የግምገማውን ሙሉ ወጪ ይሸፍናል ወይም እያንዳንዱ መንግሥት ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል ለ ሥር የተጠየቁ መስፈርቶችን ለማሟላት ከመንግሥት፣ ከአከባቢው አስተደደር፣ ከፌዴራል እና ከግል ምንጮች የሚያገኛቸውን ማናቸውንም ሀብቶች በመጠቀም ከዚህ በፊት ከተጠቀሰው የድንጋጌው ክፍል ለ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እርስዎን ወጪ ሳይጠይቅ በሌላ መንገድ ግምገማው መካሄዱን ያረጋግጣል ማለት ነው።

## በመንግሥት ወጪ ለሚደረገው ግምገማ የወላጅ መብት

በአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል የተደረገውን ግምገማ ካልተቀበሉ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ ልጅዎ በመንግሥት ወጪ ነጻ የሆነ የትምህርት ግምገማ እንዲደረግለት የማስደረግ መብት አለዎት፡-

1. ልጅዎ በመንግሥት ወጪ ነጻ የትምህርት ግምገማ እንዲደረግለት ከጠየቁ የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ያለ አንዳች መዘግየት፡- (ሀ) ለልጅዎ ያደረገው ግምገማ ተገቢ በሆነ መንገድ የተካሄደ ስለመሆኑ እንዲሰማለት አቤቱታውን ያቀርባል፤ **ወይም** (ለ) የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር አቤተታውን ካዳመጠ በኋላ ለልጅዎ የተደረገው ግምገማ የአከባቢውን የትምህርት አስተዳደር መስፈርት እንደማያሟላ ካሳየ በመንግሥት ወጪ ነጻ የትምህርት ግምገማ ይደረግለታል።
2. የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር በጽሁፍ ያቀረበው ሕጋዊ ቅሬታው እንዲሰማለት ከጠየቀና የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር በልጅዎ ላይ ያደረገው ግምገማ ተገቢ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ አሁንም ነጻ የትምህርት ግምገማ የማስደረግ መብት አለዎት፣ ነገር ግን ወጪውን መንግሥት አይሸፍንም።
3. ለልጅዎ ነጻ የትምህርት ግምገማ እንዲደረግ ከጠየቁ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የእርሱን/እርሷን ግምገማ ለምን እንዳልተቀበሉ ሊጠይቅዎ ይችላል። ነገር ግን የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ግምገማውን ላለመቀበልዎ ማብራሪያ እንዲሰጡ መጠየቅም ሆነ ምክንያታዊ ባልሆነ ሁኔታ ልጅዎ በመንግሥት ወጪ ግምገማ እንዳይደረግለት/ላት ማዘግየት ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ያደረገውን ግምገማ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ሲል በጽሁፍ ያቀረቡት ሕጋዊ አቤቱታ እንዳይሰማ ማድረግ አይችልም።

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር በልጅዎ ላይ ግምገማ በሚያደርግበት በእያንዳንዱ ጊዜ በግምገማው ውጤት ካልተስማሙ አንድ ጊዜ ብቻ በመንግሥት ወጪ ግምገማ የማስደረግ መብት አለዎት።

## በወላጅ ጥያቄ የሚደረጉ ግምገማዎች

ለልጅዎ በመንግስት ወጪ የተደረገውን ነጻ የትምህርት ግምገማ ውጤት ከተቀበሉ ወይም በግል የተደረገውን የግምገማ ወጪ ከአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ክፍል ጋር ከተጋሩ፡-

1. ለልጅዎ የተደረገው ግምገማ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለነጻ የትምህርት ግምገማ ያስቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ፣ ለሁሉም ሰው ተደራሽ የሆነ ነጻና ተገቢ ትምህርትን ማቅረብን (FAPE) በተመለከተ በሚደረግ በማንኛውም ውሳኔ የአከባበው የትምህርት አስተዳደር ውጤቶቹን መቀበል አለበት፤ **እና**
2. እርስዎ ወይም የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ልጅዎን በተመለከተ ግምገማውን በሕግ ፊት እንደ ማስረጃ ማቅረብ ይችላል።

## ጉዳዮችን የሚያዳምጡ ባለሥልጣናት ግምገማዎችን እንዲያደርጉ ጥያቄዎችን ማቅረብ

ጉዳይን ሰሚ ባለሥልጣን ጉድለት/ውስንነት ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ልዩነት

የሚፈታበት ህጋዊ ሂደት አካል በማድረግ ለልጅዎ ነጻ የሆነ የትምህርት ግምገማ እንዲደረግ ከጠየቀ የግምገማው ወጪ የመንግሥት ወጪ መሆን አለበት።

### የአከባቢ የትምህርት አስተዳደር ያስቀመጣቸው መስፈርቶች

ነጻ የትምህርት ግምገማ የሚደረገው በመንግሥት ወጪ ከሆነ ግምገማው የተደረገበትን ቦታና የፈታኙን ብቃት ጨምሮ የግምገማው ውጤት የተገኘባቸው መስፈርቶቹ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ግምገማ እንዲደረግ ተነሳሽነቱን ሲወስድ ከሚጠቀማቸው መስፈርቶች ጋር ተመሳሳይ መሆን አለባቸው (እነዚያ መስፈርቶች እርስዎ ነጻ የትምህርት ግምገማ ለማግኘት ካለዎት መብት ጋር እስኪጣጣሙ ድረስ)። ከላይ ከተጠቀሱት መስፈርቶች በስተቀር በመንግሥት ወጪ ከሚደረገው ነጻ የትምህርት ግምገማ ጋር በተገናኘ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በሁኔታዎችና የጊዜ ገደቦች ላይ ጫና አያደርግም።

## *የመረጃ ምስጢራዊነት*

### ትርጉሞች

***የመረጃ ምስጢራዊነት*** ከሚለው ርዕስ ሥር ጥቅም ላይ እንደዋለው ፦

- *ጥፋት (ውድመት) ማለት* አካላዊ ውድመት ወይም መረጃው በግል መታወቅ እንዳይችል ለማድረግ አንድን ግለሰብ ከሌሎች የሚለዩ የግል መለያዎችን ከመረጃ ውስጥ ማስወገድ ማለት ነው።
- *ተመዝግበው ያሉ የትምህርት መረጃዎች* ማለት የልጆች የሞት መጠን ጥናት (CFR) በሚል ሰነድ ውስጥ "የትምህርት መረጃዎች" በሚል ሥር (34 CFR Part 99) እና የቤተሰብ የትምህርት መብቶችንና ለብቻቸው መሆንን የሚተገብሩ ደንቦች በሚል አዋጅ ውስጥ (1974, 20 U.S.C. 1232g (FERPA)) ተመዝግበው ያሉ ነገሮች ናቸው።
- *ተሳታፊ ወኪል ማለት* ማንኛውም አንድን ግለሰብ ከሌሎች የሚለዩ የግል መለያዎችን የሚሰበስብ፣ የሚጠብቅ ወይም የሚጠቀም ወይም ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል ለ ሥር ያለው መረጃ የሚገኝበት የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል፣ ወኪል ወይም ተቋም ነው።

### በግል ተለይቶ መታወቅ የሚችል

*በግል ተለይቶ መታወቅ የሚችል* ማለት መረጃ ሆኖ የሚከተሉትን ነገሮች የሚያሟላ ነው፦

ሀ. የልጅዎ ስም፣ እንደ ወላጅ የእርስዎ ስም ወይም የሌላ የቤተሰብ አባል ስም ያለበት፤
ለ. የልጅዎ አድራሻ ያለበት፤
ሐ. እንደ የልጅዎ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ወይም የተማሪ ቁጥር ያለበት የግል መለያ፤ ወይም
መ. ልጅዎን ምክንያታዊ በሆነ እርግጠኝነት ለይቶ ማወቅ እንዲቻል የሚያደርጉ የግል ባህርያት ወይም መረጃዎች ዝርዝር ማለት ነው።

### ለወላጆች ማሳወቅ

የኔቫዳ ትምህርት ክፍል የሚከተሉትን ነጥቦች ጨምሮ ግለሰቡ ከሌሎች ተለይቶ እንዲታወቅ የሚያደርጉ መረጃዎች ምስጢራዊ ስለመሆናቸው ለወላጆች በበቂ ሁኔታ ማሳወቅ አለበት፦

1. በዚህ ግዛት ውስጥ ላሉ የተለያዩ ሕዝቦች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ነገሮችን እንዲያውቁ የተደረጉበት ደረጃ መግለጫ፤
2. ግላዊ መለያ መረጃዎች የተጠበቁላቸው ልጆች፣ የተፈለጉ የመረጃ ዓይነቶች፣ መረጃውን ለመሰብሰብ የግዛቱ መንግሥት ለመጠቀም የሚያስበቸው ዘዴዎች (መረጃው የተሰበሰበባቸውን ምንጮች ጨምሮ)፣ እና መረጃዎቹ ለምን ጥቅም እንደሚውሉ የሚገልጽ መግለጫ፤
3. አንድን ግለሰብ ከሌሎች የሚለየውን የግል መረጃ ማስቀመጥን፣ ለሶስተኛ ወገን ማሳወቅን፣ መጠበቅን እና

ማጥፋትን በተመለከተ ተሳታፊ ወኪሎች መከተል ስላለባቸው ፖሊሲዎችና የአሰራር ቅደም ተከተሎች ማጠቃለያ፣ **እና**

4. የቤተሰብ የትምህርት መብቶችና ለብቻቸው መሆን በሚል ሥር የተዘረዘሩ መብቶችንና የመተግበሪያ ደንቦችን ጨምሮ ይህን መረጃ በተመለከተ የሁሉም ወላጆችና ልጆች መብቶች መግለጫ (FERPA and its implementing regulations in 34 CFR Part 99.)

ማንኛውም ዋና የመለየት፣ ቦታ የማመልከት፣ ወይም የመገምገም ተግባር ከመፈጸሙ በፊት (ደግሞ "ልጅን ማግኘት" ተብሎ የሚታወቀው), ተግባሩ በሚከናወንበት ግዛት በሙሉ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅነት ያላቸው አገልግሎቶች የሚያስፈልጉአቸው ልጆች ያሉበትን ቦታ ለወላጆች በበቂ ሁኔታ ለማሳወቅ በሚችል በቂ የመረጃ ዝውውር ለማመልከት፣ ለይቶ ለማሳወቅና ለመገምገም ማስታወቂያው በጋዜጣ ወይም በሌላ መገናኛ ዘዴ ወይም በሁለቱም ታትሞ መውጣት ወይም መታወጅ አለበት።

## ለመረጃ ተደራሽ የመሆን (መረጃን የማግኘት) መብቶች

የአከባቢው የትምህርት አስተደደር የተሰበሰቡ፣ የተጠበቁ ወይም ውስንነት (ጉድለት) ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ባለው መሰረት በአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ጥቅም ላይ የዋሉትን ከልጅዎ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውንም ትምህርታዊ መዝገቦች እንዲፈትሹና እንዲመረምሩ ሊፈቅድልዎ ይገባል። በአከባቢው ያለው የትምህርት አስተዳደር በልጅዎ ላይ የተጻፈውን መረጃ ለመመርመርና ለመፈተሽ ያልተገባ መዘግየትን በማስወገድና ለልጅ በግል ደረጃ በሚዘጋጅ የትምህርት ፕሮግራም ፊት ወይም በማንኛውም ገለልተኛ መደበኛ የሕግ ሂደት (ውሳኔ ሰጭ ስብሰባን ወይም እርምትን/ቅጣትን በተመለከተ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ማድመጥን ጨምሮ) እንዲታይልዎ ከጠየቁት ከእርስዎ ጥያቄ ጋር መስማማት አለበት፣ ይህም እርስዎ ጥያቄ ካቀረቡ ከ45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ መሆን አለበት። የትምህርት መዝገቦችን ለመመርመርና ለመከለስ/ለመገምገም ያለዎት መብት የሚከተሉትን ነገሮች ያካትታል፡-

1. መዝገቦቹን በተመለከተ ማብራሪያዎችና ትርጉሞች እንዲሰጡዎ ላቀረቡአቸው ምክንያታዊ ጥያቄዎች ከአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል መልስ ለማግኘት ያለዎት መብት፤
2. የሰነዶቹን ቅጂዎች ካላገኙ በቀር መዝገቦቹን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ መመርመርና መፈተሽ የማይችሉ ከሆነ የአከባቢውን የትምህርት አስተዳደር የመጠየቅ መብት፤ **እና**
3. ወኪልዎ መዝገቦቹን እንዲመረምርና እንዲከልስ/እንዲገመግም ለማድረግ ያለዎት መብት

እንደ አሳዳጊነት ወይም መለየትና ፊቺ ላሉ ጉዳዮች ሥራ ላይ እየዋለ ባለው የግዛቱ የመንግሥት ሕግ መሰረት ሥልጣን እንደሌለዎ ካልተመከሩ በቀር የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ልጅዎን በተመለከተ መዝገቦችን የመመርመርና የመገምገም ስልጣን እንዳለዎ አድርጎ ይመለከታል።

## የተደራሽነት መረጃ የያዘ ፋይል (መዝገብ)

እያንዳንዱ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለተሰበሰቡ፣ ለተጠበቁ ወይም ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸውን ግለሰቦችን የሚመለከቱ የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ጥቅም ላይ ለዋሉ የትምህርት ሰነዶች ተደራሽነትን እያገኙ ያሉ ባለ ድርሻዎችን (በወላጆችና ሥልጣን ባላቸው የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሰራተኞች ተደራሽ ከሆኑት በቀር) ፣ የባለድርሻውን ስም፣ መዝገቡን እንዲያይ የተደረገበት ቀንና ዓመተ ምህረት እና ባለ ድርሻው መዝገቡን (ሰነዱን) እንዲጠቀም ሥልጣን የተሰጠበትን ዓላማ ጨምሮ መዝግቦ ማስቀመጥ አለበት።

## ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆችን ጉዳዮች የያዙ ፋይሎች (መዝገቦች)

ማንኛውም የትምህርት መዝገብ ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆችን መረጃ ካካተተ የእነዚያ ልጆች ወላጆች ከልጃቸው ጋር የተገናኘውን መረጃ ብቻ የመመርመርና የመፈተሽ ወይም ስለዚህ መረጃ ብቻ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው።

**የመረጃ ዓይነቶችና ቦታዎች ዝርዝር**

እያንዳንዱ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሲጠየቅ ስለተሰበሰቡ፣ ስለተጠበቁ ወይም በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጥቅም ላይ ስለዋሉ የትምህርት መዝገብ ዓይነቶች ዝርዝር ሊሰጥዎ ይገባል።

**ክፍያዎች**

ክፍያው እነዚያን መዝገቦች ውጤታማ በሆነ ሁኔታ የመመርመርና የመፈተሽ መብትዎን እንዳይጠቀሙ ካልከለከለዎት በቀር እያንዳንዱ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ለእርስዎ ስለ ተሰሩ መዝገቦች ቅጂዎች ሊያስከፍልዎ ይችላል። የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያለውን መረጃ ለመፈለግ ወይም የጠፋውን ለመመለስ ላያስከፍል ይችላል።

**በወላጅ ጥያቄ በፋይሎች (መዝገቦች) ላይ የሚደረግ ማሻሸያ**

በትምህርት መዝገቦች ውስጥ ስለ ልጅዎ የተሰበሰበው፣ የተጠበቀው ወይም ውስንነት (ጉድለት) ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያለው መረጃ ትክክል አለመሆኑን፣ ወደ ስህተት የሚመራ መሆኑን ወይም የልጅዎን ለብቻ የመሆንን ወይም ሌሎች መብቶችን የሚጥስ ከሆነ ወይም ይጥሰል ብለው ካመኑ መረጃውን የሚጠብቀውን የአከባቢውን የትምህርት አስተዳደር መረጃውን እንዲቀይር መጠየቅ ይችላሉ። የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጥያቄዎን በተቀበለ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በጠየቁት መሰረት መረጃውን ለመቀየር ወይም ላለመቀየር መወሰን አለበት። የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በጥያቄዎ መሰረት መረጃውን መለወጥ እምቢ ካለ እምቢ ስለማለቱ ለእርስዎ መንገር ያለበት ሲሆን ለዚሁ ዓላማ የመሰማት (የመደመጥ) ዕድል በሚል ሥር ጉዳይዎን የማሰማት ዕድል እንዳለዎ ሊነግርዎት ይገባል።

**የመደመጥ (የመሰማት) ዕድል**

ልጅዎን በተመለከተ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሲጠየቅ በትምህርት መዝገቦች ውስጥ ያለው ትክክለኛ ያልሆነ፣ ወደ ስህተት የሚመራ ወይም ለብቻ የመሆንን ወይም ሌሎች የልጅዎን መብቶች የሚጥስ መሆኑን ለማረጋገጥና መረጃውን ለመቃወም የመሰማት ዕድል ሊሰጥዎ ይገባል።

**የመደመጥ/የመሰማት ቅደም ተከተሎች**

በትምህርት መዝገቦች ላይ በሚቀርበው መረጃ ላይ ተቃውሞ መሰማት ያለበት የቤተሰብ የትምህርትና ለብቻ የመሆን መብቶችን በሚተገብሩ  ዳንቦች ውስጥ በተቀመጡ የመሰማት ቅደም ተከተሎች መሰረት ነው።

**ጉዳይዎን የመስማት ውጤት**

ከመስማት ሂደት የተነሣ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መረጃው ስህተት ያለበት፣ ወደ ስህተት የሚመራ ወይም የልጁን ለብቻ የመሆንን ወይም ሌሎች መብቶችን የሚጥስ ከሆነ በዚህ መሰረት መረጃውን ቀይሮ ለእርስዎ በጽሁፍ ሊያሳውቅ ይገባል። ከመስማት ሂደት የተነሣ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መረጃው ስህተት ያለበት፣ ወደ ስህተት የሚመራ ወይም የልጁን ለብቻ የመሆንን ወይም ሌሎች መብቶችን የሚጥስ ከሆነ ስለ ልጅዎ በሚያስቀምጣቸው መዝገቦች ውስጥ በመረጃው ላይ አስተያየት የሚሰጥ አረፍተ ነገር ወይም ከአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጋር የማይስማሙባቸውን ማናቸውንም ምክንያቶች የማስቀመጥ መብት እንዳለዎ ሊነግርዎ ይገባል። በልጅዎ መዝገብ ውስጥ የተቀመጠ የዚህ ዓይነት ማብራሪያ፡-

1. መዝገቡ ወይም ተቃውሞ የገጠመው ክፍል በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እስከተጠበቀ ድረስ የልጅዎ መዝገቦች አካል ሆኖ መጠበቅ አለበት፤ **እና**
2. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የልጅዎን መዝገቦች ወይም ተቃውሞ የቀረበበትን ክፍል ለሌላ አካል ካሳወቀ ለዚያ አካል ማብራሪያውንም ጭምር ማሳወቅ አለበት።

## አንድ ግለሰብ ተለይቶ የሚታወቅበትን መረጃ ለሌሎች አካላት ለማሳወቅ መስማማት

መረጃው በትምህርት መዝገቦች ውስጥ ከሌለ እና የቤተሰብ የትምህርት መብቶችንና ለብቻ መሆንን በሚተገብሩ ዳንቦች ሥር ያለውን አሰራር ሳይከተል ያለ ወላጅ ስምምነት ከተፈቀደ፣ ግለሰቡ ተለይቶ የሚታወቅበት መረጃ በጉዳዩ ከሚሳተፉ ወኪሎች ባለሥልጣናት ውጭ ለሌሎች አካላት ከመገለጹ በፊት የእርስዎ ስምምነት መገኘት አለበት። ከዚህ በታች በተገለጹ ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር ግለሰቡ ተለይቶ የሚታወቅበት መረጃ ውስንነት (ጉድለት) ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያሉ ዓላማዎችን ለማሳካት ሲባል በጉዳዩ ለሚሳተፉ ወኪሎች ባለሥልጣናት ከመለቀቁ በፊት የእርስዎ ስምምነት አይፈለግም። ለሽግግር አገልግሎቶች የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለሚሰጡ ወይም ለሚከፍሉ ተሳታፉ ወኪሎች ባለሥልጣናት ግለሰቡ ተለይቶ የሚታወቅበት መረጃ ከመለቀቁ በፊት የእርስዎ ወይም በአገሩ ሕግ የአብላጫ ዕድሜ በመድረሱ ብቁ የሆነ ልጅዎ ስምምነት መገኘት አለበት። ልጅዎ እርስዎ ከሚኖሩበት አከባቢ ውጭ በሆነ የትምህርት አስተዳደር ውስጥ በግል ትምህርት ቤት ካለ ወይም ወደ ግል ትምህርት ቤት ሊገባ ከሆነ ልጅዎ ተለይቶ የሚታወቅበት ማንኛውም መረጃ የግል ትምህርት ቤቱ ባለበት አከባቢ ባሉ ባለሥልጣናትና እርስዎ በሚኖሩበት አከባቢ ባሉ ባለሥልጣናት መካከል ከመለቀቁ በፊት የእርስዎ ስምምነት መገኘት አለበት።

## ከአደጋ መጠበቂያዎች

እያንዳንዱ የአከባቢ ትምህርት አስተዳደር አንድ ግለሰብ ተለይቶ የሚታወቅባቸውን መረጃዎች በሚሰበስብበት፣ በሚያከማችበት፣ በሚገልጥበትና በሚያጠፋበት ደረጃዎች ምስጢራዊነታቸውን መጠበቅ አለበት። በእያንዳንዱ የአከባቢ ትምህርት አስተዳደር ክፍል አንድ ግለሰብ ተለይቶ የሚታወቅባቸው ማረጃዎች በምሥጢራዊነት መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ አንድ ባለሥልጣን ኃላፊነት መውሰድ አለበት። አንድ ግለሰብ ተለይቶ የሚታወቅባቸውን መረጃዎች የሚሰበስቡ ወይም የሚጠቀሙ ግለሰቦች በሙሉ ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር እና የቤተሰብ የትምህርት መብቶችንና ለብቻ የመሆንን መብት የሚተገብሩ ደንቦችን በተመለከተ የኔቫዳን ፖሊሲዎችና የአሰራር ቅደም ተከተሎችን የሚመለከት ሥልጠና ወይም ትምህርት መውሰድ አለባቸው። እያንዳንዱ የአከባቢ ትምህርት አስተዳደር ሕዝብ መመርመር እንዲችል አንድን ግለሰብ ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን የሚመለከቱ በወቅቱ በአከባቢው ያሉ ሰራተኞችን ስምና ሀላፊነቶች መጠበቅ አለበት።

## መረጃን ማጥፋት

የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር የተሰበሰበው፣ የተጠበቀውና ጥቅም ላይ የዋለው አንድን ግለሰብ ለይቶ ለማወቅ የሚያችል መረጃ ለልጅዎ የትምህርት አገልግሎቶችን ለመስጠት አስፈላጊ የማይሆንበትን ጊዜ ሊነግርዎ ይገባል። መረጃው በእርስዎ ጥያቄ መጥፋት አለበት። ነገር ግን የልጅዎ ስም፣ አድረሻና የስልክ ቁጥር፣ ክፍሉ/ሏ፣ የክፍል ክትትል መዝገብ፣ የተከታተለው/የተከታተለችው ክፍል፣ የጨረሰው/የጨረሰችው የክፍል ደረጃ፣ እና ትምህርቱን/ትምህርቷን የጨረሰበት/የጨረሰችበት ዓመት ቋሚ መዝገብ ያለ አንዳች ገደብ ሊጠበቅ ይችላል።

## ጉድለት (ውስንነት) ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት በሚፈታበት ህጋዊ ሂደት መካከል እና የመንግሥት ቅሬታ/አቤቱታ በሚቀርብባቸው ቅደም ተከተሎች መካከል ያለው ልዩነት

ውስንነት (ጉዳት) ያለባቸው ግለሰቦችን በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ለ ሥር ያሉ ደንቦች ለመንግሥት አቤቱታዎችና አቤቱታዎችን በጽሁፍ ስለማቅረብና አቤቱታዎቹ ስለሚፈቱበት ሁኔታ የተለያዩ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን አስቀምጧል። ከዚህ በታች እንደተብራራው የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር፣ የኔቫዳ ትምህርት ክፍል፣ ወይም ማንኛውም የሕዝብ ወኪል በክፍል ለ ሥር ካሉ መስፈርቶች መካከል የትኛውንም ስለመጣሱ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የውንጀላ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። ውስንነት ያለበትን ልጅ ስለመለየት፣ ስለመገምገም ወይም ስለመመደብ፣ ወይም ለሁሉም ተደራሽ መሆን ያለበትን ነጻና ተገቢ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም ለልጁ ለማቅረብ ከሚቀርብ ሀሳብ ጋር በተገናኘ በማንኛውም ጉዳይ ላይ አቤቱታውን ማቅረብ የሚችለው እርስዎ ወይም የአከባቢዎ የትምህርት አስተዳደር ብቻ ነው። የጊዜ ገደቡ ተገቢ በሆነ ሁኔታ ካልተራዘመ በቀር የኔቫዳ የትምህርት አስተዳደር የመንግሥትን አቤቱታ በ60 ቀናት ውስጥ መፍታት ያለበት ሲሆን ጉድለት (ውስንነት) ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት የሚፈታበትን ህጋዊ ሂደት የሚመራው ገለልተኛ ባለሥልጣን በጽሁፍ የቀረበውን አቤቱታ በመስማት (በውሳኔ ስብሰባ ወይም በሽምግልና ካልተፈታ በቀር) የውሳኔው ወቅት ካበቃ በኋላ በዚህ ሰነድ ውስጥ **የውሳኔ ሂደት** ከሚለው ሥር በተገለጸው መሰረት በጽሁፍ የቀረበ ውሳኔን በ45 ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት። ሰሚው ባለሥልጣን በእርስዎ ጥያቄ መሰረት ለተወሰነ ጊዜ ካላራዘመ ወይም በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል ጥያቄ ካልቀረበ በቀር ይህ ሊሆን አይችልም። የመንግሥት አቤቱታና አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ፣ ውሳኔ ማቅረብና የማድመጥ ሂደቶች ከዚህ በታች በሙላት ቀርበዋል።

### የመንግሥት ቅሬታ/አቤቱታ ማቅረቢያ ቅደም ተከተሎችን ወስዶ የራስ ማድረግ

### አጠቃላ

የኔቫዳ የትምህርት ክፍል ለሚከተሉት ጉዳዮች በጽሁፍ የተዘጋጁ የአሰራር ቅደም ተከተሎች ሊኖሩት ይገባል፡-

1. ድርጅት ወይም ከሌላ ግዛት የሆነ ግለሰብ የሚያቀርባቸውን ቅሬታዎች/አቤቱታዎች ጨምሮ ማንኛውንም ቅሬታ/አቤቱታ የመፍታት፤
2. ከኔቫዳ የትምህርት ክፍል አቤቱታን የማቅረብ፤ **እና**
3. የወላጆች ሥልጠናንና የመረጃ ማዕከሎችን፣ የመከላከልና የጥብቅና ወኪሎችን፣ ነጻ የሆኑ የመኖሪያ ማዕከሎችን እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው አካላትን ጨምሮ የመንግሥትን አቤቱታ የማቅረብ ቅደም ተከተሎችን ለወላጆችና ፍላጎት ላላቸው ሌሎች ግለሰቦች በስፋት የማሰራጨት

### ተገቢ የሆኑ አገልግሎቶች ስለመነፈጋቸው የተሰጡ መፍትሄዎች

የኔቫዳ የትምህርት ክፍል ተገቢ የሆኑ አገልግሎቶችን መስጠት ባለመቻሉ መንግሥት ያቀረበውን አቤቱታ ለመፍታት የኔቫዳ ትምህርት ክፍል በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ መልስ መስጠት አለበት፡-

1. የልጁን ፍላጎቶች ለማሟላት ተገቢ የሆኑ የእርምት እርምጃዎችን ጨምሮ ተገቢ አገልግሎቶችን መስጠት አለመቻል፤ **እና**
2. ውስንነት (ጉድለት) ላለባቸው ልጆች በሙሉ ወደ ፊት ተገቢ አገልግሎት ለማቅብ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

### ዝቅተኛው የመንግሥት ቅሬታ/አቤቱታ ማቅረቢያ ቅደም ተከተሎች

### የጊዜ ገደብ፤ ዝቅተኛ የአሰራር ቅደም ተከተሎች

የኔቫዳ የትምህርት ክፍል በግዛቱ ቅሬታ/አቤቱታ ማቅረቢያ ቅደም ተከተሎች ውስጥ አቤቱታው ከቀረበ በኋላ የ60 ቀናት የጊዜ ገደብ ማካተት አለበት፡-

1. የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ከወሰነ በቦታው የሚደረግ ነጻ ምርመራ ማካሄድ

አለበት፤

2. አቤቱታ አቅራቢው በአቤቱታው ላይ ለቀረቡ ውንጀላዎች ተጨማሪ መረጃን በቃል ወይም በጽሁፍ እንዲያቀርብ ዕድል መስጠት አለበት፤
3. በትንሹ የሚከተሉትን ነገሮች ጨምሮ ለአቤቱታው ምላሽ እንዲሰጥ ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ዕድል መስጠት አለበት፡- (ሀ) በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል ምርጫ ስሞታውን ለመፍተት ሀሳብ ማቅረብ፤ **እና** (ለ) አቤቱታ ያቀረበው ወላጅና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በፈቃደኝነት በእርቅ ሥርዓት እርቅ በመፈጸም ሥራ እንዲሳተፉ ዕድል መስጠት፤
4. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ውስንነት ያለባቸውን ልጆች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ውስጥ ያለውን መስፈርት እየጣሰ መሆን ስለአለመሆኑ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች በሙሉ መመርመር፤ **እና**
5. ለአቤቱታ አቅራቢው በአቤቱታው ውስጥ ላቀረበው ለእያንዳንዱ ውንጀላ የሚከተሉትን ነገሮች የያዘ የጽሁፍ ውሳኔ መስጠት፡- (ሀ) የጭብጦችንና የማጠቃለያዎችን ግኝቶች፤ **እና** (ለ) ለኔቫዳ ትምህርት ክፍል የመጨረሻ ውሳኔ ምክንያቶችን መስጠት።

## ጊዜን ማራዘም፤ የመጨረሻ ውሳኔ፤ ሥራ ላይ ማዋል (መተግበር)

ከላይ የተገለጹት የኔቫዳ ትምህርት ክፍል የአሰራር ቅደም ተከተሎች፡-

1. በሚከተሉት ምክንያቶች ለ60 ቀናት የጊዜ ገደብ የማራዘም ፍቃድ መስጠት ያለበት፡- (ሀ) የአንድ ግዛት አቤቱታን በተመለከተ የተለዩ ሁኔታዎች ሲኖሩ፤ **ወይም** (ለ) ወላጅና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ወይም በጉዳዩ በፈቃደኝነት የተሳተፈው የሕዝብ ወኪል ጉዳዩን በሽምግልና ወይም በሌሎች ግጭት በሚፈተባቸው ዘዴዎች ለመፍታት ጊዜውን ለማራዘም ፈቃደኛ ሲሆኑ።
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚከተሉትን ነገሮች በማካተት የኔቫዳ የትምህርት ክፍል የመጨረሻ ውሳኔን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን ማካተት፡- (ሀ) የቴክኒክ እገዛ ተግባራትን፤ (ለ) ድርድርን፤ **እና** (ሐ) ከስምምነት ላይ ለመድረስ የእርምት ተግባሮችን።

## የመንግስት አቤቱታዎችና ጉድለት/ውስንነት ባለበት የተማሪ ወላጅና በአከባቢው አስተዳደር መካከል ያሉ ልዩነቶች የሚፈቱበት ህጋዊ ሂደት

ከዚህ በታች አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ ከሚለው ርዕሰ ሥር እንደቀረበው ውስንነት ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት ለሚፈታበት ሂደት ተገዥ የሆነ በጽሁፍ የቀረበ የመንግስት አቤቱታ ከተወሰደ ወይም የመንግሥት አቤቱታው ከሚይዛቸው በርካታ ጉዳዮች መካከል አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑት የሚደመጠው አቤቱታ አካል ከሆኑ የኔቫዳ ትምህርት ክፍል የማድመጥ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ የመንግሥትን አቤቱታ ወይም ውስንነት (ጉዳት) ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ልዩነት የሚፈታበትን ሂደት ወደ ጎን መተው አለበት። በአገር አቤቱታ ውስጥ አቤቱታን በጽሁፍ የማቅረብ አካል ያልሆነው ማንኛውም ጉዳይ መፈታት ያለበት የጊዜ ገደብንና ከላይ የተገለጹ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን በመጠቀም ነው። በመንግስት አቤቱታ ውስጥ የተነሣ ጉዳይ አስቀድሞውኑ ጉድለት/ውስንነት ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ባለው ልዩነት በሚፈታበት ሂደት ተመሳሳይ አካላትን (እርስዎንና የአከባቢውን የትምህርት አስተዳደር) በማሳተፍ ተወስኖ ከሆነ፣ የሂደቱ ውሳኔ አስገዳጅ ይሆናል። የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የሂደቱን ውሳኔ ለመተግበር አለመቻል በኔቫዳ የትምህርት ክፍል መፈታት አለበት።

## አቤቱታን/ ቅሬታን ማስገባት

ድርጅት ወይም ግለሰብ ከላይ በተገለጹ የአሰራር ቅደም ተከተሎች ተጽፎ የተፈረመበትን የመንግሥት አቤቱታ ማስገባት ይችላል። የመንግሥት አቤቱታ የሚከተሉትን ነገሮች ማካተት አለበት፡-

1. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ውስንነት (ጉድለት) ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያለውን መስፈርት ወይም ደንቦቹን መጣሱን የሚገልጽ አረፍተ ነገር፤
2. አረፍተ ነገሩ የተመሰረተባቸውን ጭብጦች (እውነታዎች)፤
3. ለአቤቱታው ፊርማና የግንኙነት መረጃ፤ እና
4. በተጠቀሰው ልጅ ላይ ጥሰቶች ተፈጽመዋል ብለው ውንጀላ የሚያቀርቡ ከሆነ፡-
   ሀ. የልጁ ስምና የመኖሪያ አድራሻው፣
   ለ. ልጁ እየተማረበት ያለው የትምህርት ቤቱ ስም፤
   ሐ. ቤት የለሽ ልጅ ወይም ወጣት ከሆነ ስለ ልጁ መረጃ ማግኘት የሚቻልበት የግንኙነት መረጃና ልጁ እየተማረ ያለበት ትምህርት ቤት ስም፤
   መ. የልጁ ችግር ባህሪይ መግለጫ፣ ከችግሩ ጋር የተገናኙ ጭብጦችን ጨምሮ፤ **እና**
   ሠ. አቤቱታው በቀረበበት ጊዜ አቤቱታውን እያቀረበ ላለው አካል እስከታወቀበትና እስከቀረበበት ደረጃ ድረስ ለችግሩ መፍትሄ ይሆናል የተባለው ውሳኔ።

አቤቱታው **የመንግስትን አቤቱታ የማቅረብ ቅደም ተከተሎችን የራስ ማድረግ** በሚለው ርዕስ ሥር በተገለጸው መሰረት ስሞታው ከቀረበበት ቀን ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተፈጸመውን ጥሰት በወንጀልነት ማቅረብ አለበት። አቤቱታ አቅራቢው አካል ለኔቫዳ የትምህርት ክፍል አቤቱታውን እያቀረበ ሳለ የመንግሥትን አቤቱታ እያቀረበ ያለ አካል የአቤቱታውን ቅጂ ልጁን ለሚያገለግለው ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል መላክ አለበት።

## *ሽምግልና/በሽምግልና ለማስታረቅ መሞከር*

### አጠቃላይ

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሕጋዊ አቤቱታ ከማቅረባችሁ በፊት የተነሱ ጉዳዮችን ጨምሮ  ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያለውን ማንኛውንም ነገር በማካተት አለመስማማቶችን ለመፍታት ሽምግልና እንዲኖር ማድረግ አለበት። ስለዚህ እርስዎ ሕጋዊ አቤቱታ ማቅረብ በሚለው ርዕስ ሥር በተገለጸው መሰረት ጉድለት/ውስንነት ባለበት የተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት የሚፈታበት ህጋዊ ሂደት እንዲከናወን ለመጠየቅ ህጋዊ አቤቱታ ቢያቀርቡም ባያቀርቡም ሽምግልና ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያሉ ግጭቶችን ለመፍታት ያገለግላል።

### መስፈርቶች

የሽምግልና ሂደቱ የአሰራር ቅደም ተከተሎች የሚከተሉት ነገሮችን ማከናወኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡-

1. በእርስዎ በኩልና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፤
2. ጉድለት/ውስንነት ባለበት የተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት ለሚፈታበት ህጋዊ ሂደት ያለዎትን መብት ለመንፈግ ወይም ለማዘግየት ወይም ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች የሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያሉ ሌሎች መብቶችን ለመንፈግ ጥቅም ላይ አልዋለም፤ **እና**
3. ውጤታማ የሽምግልና ቴክኒኮች በደንብ በሰለጠነ፣ ብቃት ባለውና አድልዎ በሌለበት ሽማግሌ ይከናወናል።

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የሽምግልና ሂደትን ለመከተል የማይመርጡ ወላጆችና ትምህርት ቤቶች አንዳንድ ጊዜ ለእርስዎ በሚመች ጊዜና ቦታ፣ ፍላጎት ከሌለው አካል ጋር እንዲገናኙ ዕድል የሚሰጡ የአሰራር ሂደቶችን ያዘጋጃል፡-

1. ተገቢ ከሆነ አማራጭ ግጭት ፈቺ አካል ጋር ወይም ከወላጅ ማሰልጠኛና መረጃ ማዕከል ጋር ወይም በግዛቱ ውስጥ

ካለው የሕብረተሰብ ወላጅ ማዕከል ጋር በኮንትራት ስምምነት ውስጥ ያለ፤ **እና**

2. የሽምግልና ሂደትን ጥቅሞች በማብራራት እንዲጠቀሙ የሚያደፋፍር።

የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ብቃት ያላቸው የሽምግልና ሥራ የሚሰሩና ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶችን ከመስጠት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሕጎችና ደንቦች የሚያውቁ ሰዎች ዝርዝር ሊኖረው ይገባል። የኔቫዳ ትምህርት ክፍል በሽምግልና የሚያስታርቁ ሰዎችን በዘፈቀደ፣ ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ወይም በሌሎች ፍትሃዊ በሆኑ ሁኔታዎች መምረጥ አለበት። የኔቫዳ ትምህርት ክፍል የስብሰባ ወጪዎችን ጨምሮ ለሽምግልና ሂደት ለሚያስፈልገው ወጪ ሀላፊነት ይወስዳል። በሽምግልና ሂደት ውስጥ የሚደረግ እያንዳንዱ ስብሰባ ጊዜን በጠበቀ ሁኔታ መርሀ- ግብር ሊዘጋጅለትና ለእርስዎና ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል ምቹ በሆነ ቦታ ሊካሄድ ይገባል። እርስዎና የአከበቢው የትምህርት አስተዳደር ግጭትን በሽምግልና ሂደት ከፈታችሁ ሁለቱም አካሎች ውሳኔውን ወደሚያስቀምጥ በሕግ አስገዳጅ ወደሆነ ስምምነት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

1. በሽምግልና ሂደት ወቅት የሚደረጉ ውይይቶች በሙሉ ምስጢራዊነታቸው ስለሚጠበቅ ቀጥሎ በሚኖረው ጉድለት/ውስንነት ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት በሚፈታበት ህጋዊ ሂደት ውስጥ ወይም የህግ ሂደቶች ውስጥ ጥቅም ላይ ላይውል እንደሚችል ይገልጻል፤ **እና**
2. በእርስዎና የአከባቢውን የትምህርት አስተዳደር ክፍል የማስገደድ ሥልጣን ባለው በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ወኪል ይፈረማል።

ተጽፎ የተፈረመ የሽምግልና ስምምነት በማንኛውም ግዛት ብቁ የሆነ የፍትህ ሥርዓት ባለበት ፍርድ ቤት (የዚህን ዓይነት ጉዳዮች ለመስማት በግዛቱ ህግ ስልጣን በተሰጠው) ወይም በዩናይትድ እስቴትስ የወረዳ/አውራጃ ፍርድ ቤት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። የሽምግልና ሂደት በሚካሄድበት ወቅት የተደረጉ ውይይቶች ምስጢራዊ መሆን አለባቸው። ወደ ፊት በሚደረግ ጉድለት/ውስንነት ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ልዩነትን ለመፍታት በሚደረግ ህጋዊ ሂደት ወይም በማንኛውም የፌዴራል ፍርድ ቤት የሕግ ሂደት ወይም በኔቫዳ ግዛት ፍርድ ቤት በማስረጃነት ጥቅም ላይ መዋል አይችሉም።

### የሽማግሌው ገለልተኛነት/አለማዳላት

በሽምግልና የሚያስታርቅ ሰው፡-

1. የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ተቀጣሪ ወይም በትምህርት ላይ ወይም ለልጅዎ በሚደረግ እንክብካቤ ላይ ተሳትፎ ያለው የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል ተቀጣሪ ላይሆን ይችላል፤ **እና**
2. በሽምግልና ከሚያስታርቅ ሰው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጋጭ የግል ወይም ሙያዊ ፍላጎት ሊኖረው አይገባም።

በሽምግልና ለማስታረቅ ብቁ የሚሆን ሰው የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ወይም የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ተቀጣሪ አይደለም፤ ለዚህ ምክንያቱ እርሱ ወይም እርሷ እንደ ሽምግልና አስታራቂ ደሞዝ የሚከፈለው ወይም የሚከፈላት በኔቫዳ ትምህርት አስተዳደር ክፍል ወይም በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል ስለሆነ ነው።

## *ሕጋዊ የሆነ አቤቱታ/ስሞታ ማቅረቢያ የአሰራር ቅደም ተከተሎች*

### ሕጋዊ የሆነ አቤቱታን ማቅረብ

### አጠቃላይ

እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ልጅዎን ለይቶ ማወቅን፣ መገምገምን ወይም የትምህርት ምደባን በሚመለከት ሀሳብን ከማቅረብ ወይም ካለማቅረብ ጋር ወይም ለሁሉም ተደራሽ የሆነ ነጻና ተገቢ የሆነ ትምህርት (FAPE)

ለልጅዎ ከማቅረብ ጋር በተገናኘ በማንኛውም ነገር ላይ አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል። እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር አቤቱታውን ለማቅብ መነሻ ስለሆነው የወንጀል ተግባር ካወቃችሁ ወይም ማወቅ ከነበረባችሁ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ የተከሰተ ጥሰት ከሆነ አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ ትችላላችሁ። በሚከተሉት ምክንያቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አቤቱታዎን ማቅረብ ካልቻሉ ከላይ የተሰጠው የጊዜ ገደብ በእርስዎ ላይ አይሰራም፡-

1. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በአቤቱታው ላይ የቀረቡ ጉዳዮችን ፈትቻለሁ በማለት አዛብቶ/ አሳስቶ ካቀረበ፤ **ወይም**
2. ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ለእርስዎ መሰጠት እንዳለበት የተገለጸው መረጃ እንዳይሰጥዎ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ከከለከለ።

## መረጃ ለወላጆች

እርስዎ መረጃ ከጠየቁ ወይም እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር አቤቱታን በጽሁፍ ካቀረበ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በአከባቢው ስለሚገኘው ነጻ ወይም አነስተኛ ወጪ ስለሚጠይቅ ማንኛውም የህግ ወይም ሌላ ተዛማጅ አገልግሎቶች መረጃ ሊሰጥዎ ይገባል።

## አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ

## አጠቃላይ

አቤቱታዎ እንዲሰማዎ ለመጠየቅ እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር (ወይም ጠበቃዎ ወይም የአከባቢው የትምህረርት አስተዳደር ክፍል ጠበቃ) ለሌላኛው አካል አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ አለባችሁ። አቤቱታው ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ይዘቶችን በሙሉ የያዘ ሆኖ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ መሆን አለበት። እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር፣ ማንኛችሁም አቤቱታ ካቀረባችሁ፣ የአቤቱታችሁን ቅጂ ለኔቫዳ የትምህርት ክፍል መስጠት አለባችሁ።

## የአቤቱታው ይዘት

በጽሁፍ የሚቀርብ አቤቱታ የሚከተሉትን ነገሮች ማካተት አለበት፡-

1. የልጁን ስም፤
2. ልጁ የሚኖርበትን አድራሻ፤
3. ልጁ የሚማርበትን ትምህርት ቤት ስም፤
4. ልጁ ቤት የሌለው ልጅ ወይም ወጣት ከሆነ ልጁን ማግኘት የሚቻልበት መረጃና የልጁ ትምህርት ቤት ስም፤
5. ከችግሩ ጋር የተገናኙ ጭብጦችን ጨምሮ እንዲተገበር ከቀረበው ወይም አምቢ ከተባለው ተግባር ጋር ግንኙነት ስላለው የልጁ ችግር ባህርይ መግለጫ፤ **እና**
6. በጊዜው ለእርስዎ ወይም ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እስከታወቀና እስከቀረበላችሁ ድረስ እንዲተገበር የቀረበ የመፍትሄ ሀሳብ።

## በጽሁፍ የቀረበ አቤቱታን ከመስማት በፊት ማሳወቅ ያስፈልጋል

እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር (ወይም ጠበቃዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል ጠበቃ) ከላይ የተዘረዘረውን መረጃ የሚያካትት አቤቱታ እስካላቀረባችሁ ድረስ አቤቱታችሁ ላይሰማ ይችላል።

## የአቤቱታው ብቁነት

በጽሁፍ የቀረበው አቤቱታ የመሰማቱ ሂደት ወደ ፊት እንዲቀጥል ብቁ መሆኑ መታወቅ አለበት። በጽሁፍ የቀረበውን አቤቱታ የሚቀበለው አካል (እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር) ለሚሰማው ሀላፊና ለሌላው አካል አቤቱታውን

በተቀበላችሁት በ15 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ የቀረበው አቤቱታ ከላይ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን አያሟለም በማለት በጽሁፍ ካላሳወቃችሁ በቀር በጽሁፍ የቀረበው አቤቱታ ብቁ እንደሆነ ይቆጠራል (ከላይ የተዘረዘሩ ይዘቶች የሚጠይቁአቸውን መስፈርቶች ካሟላ)። ተቀባዩ ክፍል (እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር) ማሳሰቢያውን በተቀበለበት በአምስት ቀናት ውስጥ በጽሁፍ የቀረበው አቤቱታ ብቁ አይደለም ብሎ ከቆጠረ አቤቱታውን የሚሰማው ሀላፊ በጽሁፍ የቀረበው አቤቱታ ከላይ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላት አለማሟላቱን በመወሰን ለእርስዎና ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል ወዲያውኑ በጽሁፍ ያሳውቃል።

## አቤቱታን ማሻሻል

እርስዎ ወይ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በአቤቱታው ላይ ለውጥ ማድረግ የምትችሉት በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡-

1. ሌላኛው አካል ለውጦቹን በጽሁፍ ሲያረጋግጥና በጽሁፍ የቀረበው አቤቱታ ከዚህ በታች በተገለጸው የውሳኔ ስብሰባ እንዲፈታ ዕድል ከሰጠ፤ **ወይም**
2. የማድመጥ ሂደቱ ከመጀመሩ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ የሚሰማው ኃላፊ ለውጥ እንዲደረግ ፈቃድ ከሰጠ።

አቤቱታ አቅራቢው አካል (እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር) በጽሁፍ በቀረበው አቤቱታ ላይ ለውጥ ካደረገ የውሳኔ ስብሰባው ጊዜ (አቤቱታውን በተቀበለበት 15 ቀናት ውስጥ) እና ውሳኔ የሚሰጥበት ጊዜ (አቤቱታውን በተቀበለበት 30 ቀናት ውስጥ) እንደገና የሚጀምረው ማሻሻያ የተደረገበት አቤቱታ በቀረበበት ቀን ነው።

## በጽሁፍ ለቀረበው አቤቱታ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መልስ

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በእርስዎ የጽሁፍ አቤቱታ ውስጥ ያለውን ነገር በተመለከተ ***ቀዳሚ የጽሁፍ ማሳሰቢያ*** በሚለው ርዕስ ሥር በተገለጸው መሰረት አስቀድሞ የጽሁፍ ማሳሰቢያ ካልላከልዎ፣ በጽሁፍ የቀረበውን አቤቱታ በተቀበለበት 10 ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች ያካተተ መልስ ሊልክልዎ ይገባል፡-

1. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በጽሁፍ በቀረበው አቤቱታ ላይ ለምን እርምጃ እንዲወሰድ ሀሳብ እንዳቀረበ ወይም ማቅረብ እምቢ እንዳለ ማብራሪያ፤
2. ለልጅዎ በግል የተዘጋጀው የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ኮሚቴ የተመለከታቸው ሌሎች አማራጮችና እነዚያ አማራጮች ተቀባይት ያላገኙባቸው ምክንያቶች፤
3. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እንዲተገበር ሀሳብ ላቀረበው ወይም ማቅረብ እምቢ ላለው ተግባር መሰረት አድርጎ የተጠቀመው የእያንዳንዱ ግምገማ ሂደት፣ ዳሰሳ፣ ምዝገባና ሪፖርት መግለጫ፤ **እና**
4. የአከባቢ የትምህርት አስተዳደር እንዲተገበር ሀሳብ ካቀረበው ወይም ማቅረብ እምቢ ካለው ተግባር ጋር ግንኙነት ያላቸው ሌሎች ነገሮች መግለጫ።

ከላይ ከቁጥር 1-4 ላይ በቀረቡ ነገሮች ላይ መረጃ መስጠት የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የእርስዎ በጽሁፍ የቀረበው አቤቱታ ብቁ አይደለም ብሎ ካመረጋገጥ አያግደውም።

## በጽሁፍ ለቀረበው አቤቱታ የሌላ አካል መልስ

ከላይ በጽሁፍ ለቀረበው አቤቱታ ***የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መልስ*** በሚል ንዑስ ርዕስ ሥር ከተገለጸው በስተቀር በጽሁፍ የቀረበውን አቤቱታ የሚቀበለው አካል አቤቱታውን በተቀበለበት 10 ቀናት ውስጥ ለሌላኛው አካል በአቤቱታው ውስጥ ያለውን ጉዳይ የሚመለከት መልስ መላክ አለበት።

## ሞዴል ፎርሞች

በጽሁፍ የሚቀርብ አቤቱታንና የመንግሥት አቤቱታን እንዲያቀርቡ ለመርዳት የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ሞዴል ፎርሞችን ማዘጋጀት አለበት። ነገር ግን የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ወይም የአከባቢው ትምህርት አስተዳደር እነዚህን ሞዴል ፎርሞች እንዲጠቀሙ ላይጠይቁዎ ይችላሉ። በጽሁፍ የሚቀርብ አቤቱታን ወይም የመንግሥት አቤቱታን ለማቅረብ የሚያስፈለግ መረጃ እስከያዘ ድረስ ይህንን ፎርም ወይም ሌላ ተገቢ የሆነ ሞዴል ፎርም መጠቀም ይችላሉ።

**መፍትሄ የመፈለግ ሂደት**

**የመፍትሄ ስብሰባ**

በጽሁፍ ላቀረቡት አቤቱታ ማሳሰቢያ በተቀበሉ በ15 ቀናት ውስጥ እና አቤቱታው የሚደመጥበት ሂደት ከመጀመሩ በፊት የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ከእርስዎና ከሚመለከተው አባል ወይም በአቤቱታዎ ተለይተው ስለሚታወቁ ጭብጦች የተለየ እውቀት ካላቸው ግለሰብን ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀው የትምህርት ፕሮግራም (IEP)ኮሚቴ አባላት ጋር መሰብሰብ አለበት። ስብሰባው፡-

1. የአከባቢውን የትምህርት አስተዳደር ወክሎ ውሳኔ የማስተላለፍ ሥልጣን ያለውን የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ወኪል ማካተት አለበት፤ **እና**
2. እርስዎ በጠበቃ ካልታጀቡ በቀር የአከባቢውን የትምህርት አስተዳደር ጠበቃን ላያካትት ይችላል።

ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰብን ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀው የትምህርት ፕሮግራም (IEP)ኮሚቴ አባላት በስብሰባው እንዲሳተፉ የምትወስኑት እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ናችሁ።

የስብሰባው ዓላማ የአከባቢው የትምህርት አስተደዳደር ግጭቱን ለመፍታት እድል እንዲኖረው እርስዎ በጽሁፍ ባቀረቡት አቤቱታ ላይ እና ለአቤቱታው መነሻ በሆኑ ጭብጦች ላይ ለመወያየት ነው።

የመፍትሄ ስብሰባው አስፈላጊ የማይሆንባቸው ምክንያቶች፡-

1. እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ስብሰባውን ለመተው በጽሁፍ ስትስማሙ፤ **ወይም**
2. እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ***ሽምግልና*** በሚል ርዕስ ስር በተገለጸው መሰረት የሽምግልና ሂደትን ለመጠቀም ስትስማሙ።

**ውሳኔ የሚሰጥበት ጊዜ**

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር አቤቱታዎን በጽሁፍ በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ (የመፍትሄ ሂደት በሚከናወንበት ወቅት) በሚያረካዎ መልክ ካልፈታ ልዩነቱ የሚፈታበት ህጋዊ የማድመጥ ሂደት ይከናወናል። የመጨረሻ ውሳኔን ለመስጠት የተቀመጠው የ45 ቀናት የጊዜ ገደብ ከዚህ በታች እንደተገለጸው 30ዎቹ የመፍትሄ ቀናት በመጠናቀቅ ይጀምረል። እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የውሳኔ ሂደቱን ለመተው ወይም ሽምግልናን ለመጠቀም ካልወሰናችሁ በቀር ውሳኔ በሚሰጥበት ስብሰባ ላይ አለመሳተፋችሁ በስብሰባው ለመሳተፍ እስክትስማሙ ድረስ ለውሳኔ ሂደቱ ያለውን የጊዜ ገደብ ያዘገየዋል። ምክንያታዊ ጥረቶች ካደረጉና እነዚህን ጥረቶች ከሰነዱ በኋላ የአከባቢው ትምህርት አስተዳደር በውሰኔ አሰጣጥ ስብሰባው የእርስዎን ተሳትፎ ማግኘት ካልቻለ በ30ዎቹ መፍትሄ የመስጠት ቀናት መጨረሻ ላይ አቤቱታ ሰሚው ባለሥልጣን የእርስዎን አቤቱታ ለመዝጋት ይጠይቃል። የዚህ ዓይነት ጥረቶችን የመሰነድ ሥራ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በጋራ የተስማሙበትን ጊዜና ቦታ ለማዘጋጀት ያደረጋቸውን የሚከተሉትን ዓይነት ጥረቶችም መዝግቦ መያዝ አለበት፡-

1. ጥሪ የተደረጉ ወይም ለማድረግ ጥረት የተደረገባቸው የስልክ ጥሪዎች መዝገቦችና የእነዚያ ጥሪዎች ውጤቶች፤
2. ለእርስዎ የተላኩ የግንኙነት ቅጂዎችና የተቀበሉአቸው መልሶች፤ **እና**
3. ወደ ቤትዎ ወይም ወደ ሥራ ቦታዎ የተደረጉ ጉብኝቶች መዝገብና የእነዚያ ጉብኝቶች ውጤቶች።

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በጽሁፍ ለቀረበው አቤቱታዎ ማሳሰቢያ በተቀበለበት በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ሰጭ ስብሰባን ማካሄድ ካልቻለ ወይም በውሳኔ ሰጭ ስብሰባው ላይ መሳተፍ ካልቻለ አቤቱታ የሚሰማው ሀላፊ ሂደቱ የሚሰማባቸው 45 ቀናት እንዲጀምሩ ትዕዛዝ እንዲሰጥ መጠየቅ ይችላሉ።

### በ30 ቀናት የመፍትሄ ጊዜ ላይ ማስተካከያዎች

እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ውሳኔ ሰጭ ስብሰባን ለመተው በጽሁፍ ከተስማማችሁ ሂደቱ የሚሰማባቸው 45 ቀናት በሚቀጥለው ቀን ይጀምራሉ። ሽምግልናው ወይም የውሳኔ ስብሰባው ጅምርና 30ዎቹ የመፍትሄ መፈለጊያ ቀናት ከማለቃቸው በፊት እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ምንም ዓይነት ስምምነት ማድረግ የሚቻል አይደለም ብላችሁ በጽሁፍ ከተስማማችሁ አቤቱታውን የማድመጥ ሂደት 45 ቀናት በቀጣዩ ቀን ይጀምራሉ። እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የሽምግልና ሂደትን ለመጠቀም ከተስማማችሁ በ30ዎቹ የመፍትሄ ቀናት መጨረሻ ላይ ከስምምነት ላይ እስኪደረስ ድረስ ሁለቱም አካሎች በሽምግልና ለመቀጠል በጽሁፍ መስማማት ይችላሉ። ነገር ግን እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ከሽምግልና ሂደቱ ቢወጣ፣ አቤቱታው የሚሰማባቸው 45 ቀናት በቀጣዩ ቀን ይጀምራሉ።

### መፍትሄ የመፈለግ የጽሁፍ ስምምነት

መፍትሄ በሚፈለግበት ስብሰባ ላይ ለግጭቱ ከመፍትሄ ላይ ከተደረሰ እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በሕግ አስገዳጅ ወደሆነ ስምምነት የምትገቡት፡-

1. በእርስዎና የአከባቢውን የትምህርት አስተዳደር የማስገደድ ሥልጣን ባለው የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ወኪል ሲፈረም፤ እና
2. በማንኛውም ብቃት ባለው የመንግሥት ፍርድ ቤት (የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን የመስማት ሥልጣን ያለው የመንግሥት ፍርድ ቤት) ወይም በዩናይትድ እስቴትስ የአውራጃ/ወረዳ ፍርድ ቤት ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ።

### ስምምነትን የመከለስ/የመገምገም ጊዜ

እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ከውሳኔ ስብሰባው የተነሣ ከስምምነት ላይ ከደረሳችሁ ከሁለት አንዳችሁ (እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር) ስምምነቱን ከፈረማችሁበት ቀን አንስቶ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ስምምነቱን መሰረዝ ትችላላችሁ።

## *በጽሁፍ የቀረቡ አቤቱታዎችን መስማት*

### ገለልተኛ የሆነ (አድልዎ የሌለበት) አቤቱታን የመስማት ሂደት

### አጠቃላይ

በማንኛውም ጊዜ አቤቱታ በጽሁፍ ሲቀርብ በግጭቱ ውስጥ ተሳትፎ ያላችሁ እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ከላይ **አቤቱታን በጽሁፍ የመስማት ሂደትና ውሳኔ የመስጠት ሂደት በሚሉ** ክፍሎች ውስጥ በተገለጸው መሰረት በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በተጠራ ስብሰባ ላይ ገለልተኛ የሆነ (አድልዎ የሌለበት) የመደመጥ (የመሰማት) ዕድል ማግኘት አለባችሁ።

### ገለልተኛ የሆነ (የማያዳላ) አቤቱታ ሰሚ ባለሥልጣን

አቤቱታ ሰሚ ባለሥልጣን ቢያንስ፡-

1. በትምህርት ወይም በልጅ እንክብካቤ ተሳታፊ ከሆነ የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ተቀጣሪ ሰራተኛ መሆን የለበትም። ነገር ግን ግለሰቡ/ቧ የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ተቀጣሪ የማይሆንበት/የማትሆንበት ብቸኛውም ምክንያት እርሱ/እርሷ እንደ አቤቱታ ሰሚ ባለሥልጣን ለማገልገል በኔቫዳ

የትምህርት ክፍል ተከፋይ ስለሆነ/ ስለሆነች ነው፤

2. አቤቱታው ሲሰማ ከአቤቱታ ሰሚ ባለሥልጣን ተአማኒ መሆን ጋር የሚጋጭ ግላዊ ወይም ሙያዊ ፍላጎት ሊኖረው አይገባም፤
3. እውቀት ያለውና ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች የሚመለከተውን የትምህርት ድንጋጌ፣ ይህን ድንጋጌ በተመለከተ የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ደንቦች እና ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች የሚመለከተውን የትምህርት ድንጋጌ ሕጋዊ ትርጉሞችና የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ለዚህ ድንጋጌ የሚሰጡአቸውን ሕጋዊ ትርጉሞች የሚረዳ መሆን አለበት፤ **እና**
4. አቤቱታ የመስማት ሂደትን የመምራትና ተገቢ በሆነ እና ደረጃውን በጠበቀ የህግ ልምምድ ውሳኔዎችን የማድረግና የመጻፍ እውቀትና ችሎታ ያለው መሆን አለበት።

የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ስለ እያንዳንዱ አቤቱታ ሰሚ ባለሥልጣን ብቃቶች የሚገልጹ አረፍተ ነገሮችን ጨምሮ ሰሚ ባለሥልጣን ሆነው የሚያገለግሉ ባለሥልጣናትን ስም ዝርዝር ይይዛል።

### አቤቱታ የመስማት ሂደት ርዕሰ ጉዳይ

አቤቱታ እንዲሰማ የሚጠይቀው ባለ ድርሻ አካል (እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር) ሌላኛው አካል ካልተስማማ በቀር አቤቱታን በጽሁፍ በማቅረብ ሂደት ላይ ያልተነሱ ጉዳዮችን አቤቱታ በመስማት ሂደት ላይ ላያነሳ ይችላል።

### አቤቱታ እንዲሰማ ለመጠየቅ የጊዜ ገደብ

በአቤቱታው ላይ ስለተነገው ነገር እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ስላወቀው ወይም ማወቅ ስለነበረበት ጉዳይ አቤቱታው በቀረበበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ገለልተኛ የሆነ የመስማት ተግባር እንዲፈጸም እርስዎ ወይም የአከባቢው ትምህርት አስተዳደር መጠየቅ አለበት።

### የጊዜ ገደብን በተመለከተ ሕጉ የማይመለከታቸው ነገሮች

ከሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ አቤቱታዎን በጽሁፍ ካላቀረቡ ከላይ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ለእርስዎ አይሰራም፡-

1. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እርስዎ በአቤቱታዎ እያነሱ ያሉትን ችግር ወይም ጉዳይ ፈትቻለሁ በማለት የተዛባ መረጃ ከሰጠ፤ **ወይም**
2. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ውስጥ ለእርስዎ መስጠት እንዳለበት የተቀመጠውን መረጃ ከከለከለዎ።

### የማድመጥ መብቶች

### አጠቃላይ

ቅሬታን በመስማት ሂደት ውስጥ ያለ ማንኛውም አካል (ከድስፕሊን የአሰራር ቅደም ተከተሎች ጋር የተገናኘ መስማትን ጨምሮ) ወይም የውሳኔ ይግባኞች በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር በተገለጸው መሰረት ይግባኝን በተመለከተ ገለልተኛ የሆነ ክለሳ የሚከተለውን የማድረግ መብት አለው፡-

1. በአማካሪ/ጠበቃ የመወከል፤
2. ጉድለት (ውስንነት) ያለባቸው ልጆችን ችግሮች በተመለከተ ልዩ እውቀት ወይም ስልጠና ባላቸው ሰዎች የመታጀብ ወይም የመመከር፤
3. ማስረጃ የማቅረብና ፊት ለፊት የመጋፈጥ፣ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ እና የምስክሮችን መሳተፍ የመጠየቅ፣
4. አቤቱታው ከመሰማቱ በፊት ቢያንስ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለሌላኛው አካል ያልተገለጠውን ማንኛውንም ማስረጃ እንዳያስተዋውቁ የመከልከል፤

5. አቤቱታው የተሰማበትን ቃል በቃል የተመዘገበ የጽሁፍ ወይም በምርጫዎ የኤሌክትሮኒክ መረጃን የማግኘት፤ **እና**
6. የጭብጦችንና የውሳኔዎችን የተጻፈ ወይም በምርጫዎ ኤሌክትሮኒክ መረጃን የማግኘት።

### ተጨማሪ መረጃን ማሳወቅ

አቤቱታ/ቅሬታ ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ ከመደመጡ ቢያንስ አምስት የሥራ ቀናት ቀደም ብሎ እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለእርስ በርሳችሁ እስከዚያ ቀን የተደረጉ ግምገማዎችን በሙሉ እና እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለመጠቀም በምታስቡአቸው ግምገማዎች ላይ የተሰጡ መልካም ምስክርነቶችን ማሳወቅ አለባችሁ። ቅሬታውን የሚሰማው ባለሥልጣን ከዚህ መስፈርት ጋር የማይስማማውን ማንኛውንም አካል ለሁኔታው ገጣሚ የሆነ ግምገማን ወይም ምስክርነትን ያለ ሌላኛው አካል ስምምነት እንዲያሳውቅ አይፈቅድም።

### አቤቱታ/ቅሬታ በሚሰማበት የወላጅ መብቶች

የሚከተሉት መብቶች ለወላጅ መሰጠት አለባቸው:-

1. ልጅዎ በቦታው እንዲገኝ እንዲያደርጉ፤
2. አቤቱታውን ለሕዝብ እንዲሰማ ክፍት እንዲያደርጉ፤ **እና**
3. የተሰማው አቤቱታ/ቅሬታ፣ የጭብጥ ግኝቶችና ውሳኔዎች ያለ ወጪ ተቀድተው እንዲሰጡ።

### ውሳኔዎችን መስማት

### የአቤቱታ/የቅሬታ ሰሚ ባለ ሥልጣን ውሳኔ

ልጅዎ ለሕዝብ ተደራሽ የሆነ ነጻና ተገቢ ትምህርት (FAPE) ስለማግኘት አለማግኘቱ የቅሬታ ሰሚው ባለ ሥልጣን ውሳኔ መመስረት ያለበት ቋሚ በሆነ መሰረት ላይ ነው። የአሰራር ቅደም ተከተል ጥሰቶች ስለመኖራቸው ለሚቀርቡ ውንጀላዎች ቅሬታ ሰሚው ባለሥልጣን ልጅዎ ለሁሉም ተደራሽ የሆነ ነጻና ተገቢ ትምህርት ያላገኘው የአሰራር ቅደም ተከተል ጉድለቶች፡-

1. ልጅዎ ለሕዝብ ተደራሽ የሆነ ነጻና ተገቢ ትምህርት ለማግኘት ባለው መብት ላይ ጣልቃ ገብተዋል፤
2. ለሕዝብ ተደራሽ የሆነ ነጻና ተገቢ ትምህርትን ለልጅዎ ማቅረብን በተመለከተ ውሳኔ በመስጠት ሂደት ላይ ለመሳተፍ ባለዎት ዕድል ላይ ወሳኝ በሆነ ሁኔታ ጣልቃ ገብተዋል፤ ወይም
3. የትምህርት ጥቅም መስመሩን እንዲስት አድርገዋል።

ከላይ ከተዘረዘሩት መሰናዶዎች መካከል አንዱም ቢሆን ቅሬታ ሰሚው ባለሥልጣን የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር የፌዴራል ደንቦች የአሰራር ቅደም ተከተሎች መጠበቂያ ከሚለው ክፍል ጋር እንዲስማማ ከማዘዝ እንደሚከለክል ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም። (34 CFR §§300.500 through 300.536).

**አቤቱታን/ቅሬታን በጽሁፍ የማቅረብ ሂደት፤ በጽሁፍ የሚቀርብ ቅሬታ፤ ሞዴል ፎርሞች፤ የውሳኔ ሂደቶች፤ ገለልተኛ ቅሬታን የመስማት ሂደት፣ የመስማት መብቶች እና ውሳኔዎችን መስማት** (34 CFR §§300.507 through 300.513) በሚሉ ርዕሶች ሥር ከቀረቡ መሰናዶዎች መካከል አንዱም ቢሆን ከኔቫዳ የትምህርት ክፍል ውሳኔውን ለመስማት ይግባኝ ለመጠየቅ ባለዎት መብት ላይ ተጽእኖ ማድረግ አይችልም።

### ጉድልት/ውስንነት ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት የሚፈታበት ህጋዊ ሂደት እንዲካሄድ በግል መጠየቅ

ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር በተቀመጠው የፌዴራል ደንቦች የአሰራር ቅደም ተከተሎች መጠበቂያዎች (34 CFR §§300.500 through 300.536) በሚለው ክፍል ካሉ ነገሮች አንዱም ቢሆን አስቀድመው ቅሬታዎን በጽሁፍ ካቀረቡበት ጉዳይ ሌላ ነገር ላይ ቅሬታዎን በግል ማቅረብን እንደሚከለክል ተደርጎ ሊተረጎም

አይችልም።

**ግኝቶችና ውሳኔ ለአማካሪ ቡድንና ለአጠቃላይ ሕዝብ**

የኔቫዳ ትምህርት ክፍል በግል ተለይቶ የሚታወቀውን ማንኛውንም መረጃ ካጠፋ በኋላ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለበት፦

1. አቤቱታን/ቅሬታን በመስማት ሂደት ላይ ወይም ለመንግሥት ልዩ አማካሪ ቡድን በቀረበው አቤቱታ ላይ የተገኙ ግኝቶችንና የተሰጡ ውሳኔዎችን ማቅረብ አለበት፤ እና
2. እነዚያን ግኝቶችና ውሳኔዎች ለሕዝብ እንዲደርሱ ማድረግ አለበት።

*ይግባኞች*

**የውሳኔ መጨረሻነት፤ ይግባኝ፤ ገለልተኛ ክለሳ (ግምገማ)**
**ውሳኔን የመስማት መጨረሻነት**

ጉድለት/ውስንነት ባለበት ተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት የሚፈታበት ሂደት ከተሰማ በኋላ የተሰጠው ውሳኔ (ከድስፕሊን አሰራር ቅደም ተከተሎች ጋር የተገናኘውን ውሳኔ መስማት ጨምሮ) አጥጋቢ ካልሆነ ቅሬታውን በመስማት ሂደት የተሳተፈው ማንኛውም አካል (እርስዎ ወይም የአከባቢው ትምህርት አስተዳደር) ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት ለኔቫዳ የትምህርት ክፍል ይግባኝ ማስገባት ይችላለል።

**የውሳኔዎች ይግባኝ፤ ገለልተኛ ክለሳ**

አንድ አካል (እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር) በተሰሙ ግኝቶችና ውሳኔ ካዘነ ለኔቫዳ የትምህርት ክፍል ይግባኝ ማስገባት ይችላል። ቅሬታ ሰሚ ባለሥልጣን በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው አካል ውሳኔውን ከተቀበላ በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል። ጉዳዩ የተሰማለት አካል የመጀመሪያ አቤቱታ ማሳሰቢያን ከተቀበለ በኋላ በ10 ቀናት ውስጥ መስቀለኛ ይግባኝ (የታችኛው ፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲያይ አቤት ማለት) ማስገባት ይችላል።

ይግባኝ ካለ የኔቫዳ ትምህርት ክፍል ሹም/ተቆጣጣሪ ይግባኝ በተጠየቀባቸው ግኝቶችና ውሳኔ ላይ ገለልተኛ ክለሳ/ግምገማ የሚያደርግ የመንግሥት ባለሥልጣን ይሾማል። ግምገማ/ክለሳ የሚያደርገው የመንግሥት ባለሥልጣን ግምገማውን ሲያደርግ፦

1. አቤቱታው የተሰማበትን ጠቅላላ መዝገብ መመርመር አለበት፤
2. አቤቱታው የተሰማባቸው ቅደም ተከተሎች ሂደቱ ከሚጠይቃቸው መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤
3. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ ማስረጃ መፈለግ አለበት። ተጨማሪ ማስረጃ ለማግኘት አቤቱታውን የመስማት ተግባር ከተከናወነ፣ ከላይ **የመስማት መብቶች** በሚለው ርዕስ ሥር የተገለጹ የመስማት መብቶች ሥራ ላይ መዋል አለባቸው፤
4. ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ክለሳ የሚያደርገው ሀላፊ በሚሰጠው ነጻነት በጽሁፍ ወይም በቃል ወይም በሁለቱም እንዲከራከሩ ዕድል መስጠት አለበት፤
5. ግምገማው/ክለሳው ሲጠናቀቅ ገለልተኛ የሆነ ውሳኔ መደረግ አለበት፤ **እና**
6. የተገኘው ጭብጥና ውሳኔዎች ለእርስዎና ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በጽሁፍ ወይም በምርጫችሁ በኤሌክትሮኒክ ቅጂ ሊሰጡአችሁ ይገባል።

**ግኝቶችና ውሳኔ ለአማካሪ ቡድንና ለአጠቃላይ ሕዝብ**

የኔቫዳ ትምህርት ክፍል አንድ ግለሰብ ተለይቶ የሚታወቅበትን ማንኛውንም መረጃ ካጠፋ በኋላ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለበት፡-

1. የይግባኙን ግኝቶችና ውሳኔዎች ልዩ ለሆነው የመንግሥት የትምህርት አማካሪ ቡድን መስጠት አለበት፤ **እና**
2. እነዚያን ግኝቶችና ውሳኔዎች ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ አለበት።

**የውሳኔ ክለሳ/ግምገማ መጨረሻነት**

በመንግሥት የክለሳ/ግምገማ ባለሥልጣን የተሰጠው ውሳኔ እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የመንግሥት የወሰደውን እርምጃ ካላመጣችሁ በቀር የመጨረሻው ውሳኔ ይሆናል።

## *የአቤቱታዎች መሰማትና ክለሳዎች/ግምገማዎች የጊዜ ገደብና አመቺነት*

ለውሳኔ ስብሰባዎች የተሰጡ 30 ቀናት ካለቁ በኋላ ከ45 ቀናት በላይ ሳይዘገይ፣ ወይም ለውሳኔ በተሰጡ 30 ቀናት ላይ የሚደረግ ማስተካከያ በሚል ንዑስ ርዕስ ሥር በተገለጸው መሰረት ማስተካከያ ከተደረገበት ጊዜ ማብቂያ በኋላ 45 ቀናት ሳያልፉ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር፡-

1. በይግባኝ መስማት ሂደት ከመጨረሻው ውሳኔ ላይ መደረሱን ማረጋገጥ አለበት፤ እና
2. የውሳኔው ቅጂ ለእርስዎና ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በደብዳቤ ሊደርሳችሁ ይገባል።

የኔቫዳ የትምህርት ክፍል ለክለሳ/ግምገማ ጥያቄ ከደረሰው በኋላ ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡-

1. በክለሳው/ግምገማው ላይ የመጨረሻው ውሳኔ መደረሱን ማረጋገጥ አለበት፤ **እና**
2. የውሳኔው ቅጂ ለእርስዎና ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በፖስታ ቤት መላኩን ማረጋገጥ አለበት።

እርስዎ ወይም የአከባባው የትምህርት አስተዳደር የተሰጠው ጊዜ እንዲራዘም ጥያቄ ካቀረባችሁ አቤቱታ ሰሚው ወይም ገምጋሚው ሀላፊ ከላይ ከተገለጸው ጊዜ ባሻገር (ውሳኔን ለመስማት ከተሰጡ 45 ቀናትና ውሳኔን ለመገምገም ከተሰጡት 30 ቀናት) በተለየ ሁኔታ ጊዜውን ሊያራዝም ይችላል። የቃል ክርክሮችን የሚያካትተው እያንዳንዱ የመስማትና የመገምገም ተግባር ለእርስዎና ለልጅዎ አሳማኝ በሆነ ደረጃ ምቹ በሆነ ጊዜና ቦታ መደረግ አለበት።

## *እርምጃዎችን ለመሰነድ የሚያስፈልገውን ጊዜ ጨምሮ የመንግሥት እርምጃዎች*

**አጠቃላይ**

በመንግሥት ደረጃ በተደረገው ግምገማ በተገኙ ግኝቶችና ውሳኔ የማይስማማ ማንኛውም አካል (እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር) በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ለሚፈታበት ህጋዊ ሂደት (የድስፕሊን እርምጃ የሚወሰድባቸውን የአሰራር ቅደም ተከተሎችን መስማትን ጨምሮ) ርዕስ ከሆነው ጉዳይ አንጻር መንግሥት እርምጃ እንዲወስድ የማምጣት መብት አለው። ተግባሩ ሕግን በተመለከተ ፍርድ የመስጠት ኃይል ወዳለው ብቁ ወደሆነ (የዚህን አይነት ጉዳይ ለመስማት ሥልጣን ያለው የመንግሥት ፍርድ ቤት) የመንግሥት ፍርድ ቤት ወይም የግጭቱ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ በአሜሪካ የአከባቢ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል።

**የጊዜ ውስንነት**

እርምጃውን እያመጣ ያለው አካል (እርስዎ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር) የመንግሥት ግምገማ ሀላፊን ውሳኔ ከተቀበለበት ጊዜ አንስቶ የመንግስት እርምጃ እንዲወሰድ ለመጠየቅ 90 ቀናት ይኖሩታል።

## ተጨማሪ የአሰራር ቅደም ተከተሎች

በማንኛውም የመንግሥት እርምጃ፣ ፍርድ ቤቱ፡-

1. የአስተዳደረዊ እርምጃዎችን መዝገቦች ይቀበላል፤
2. በእርስዎ ጥያቄ ወይም በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጥያቄ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ይሰማል፤ **እና**
3. ውሳኔውን በማስረጃው ጥንካሬ በመመስረት ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ የሚወስነውን እፎይታ ይሰጣል።

## የአከባቢው ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የመስጠት ኃይል

በአሜሪካ ያሉ የየአከባቢው ፍርድ ቤቶች የግጭቱን መጠን በተመለከተ ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር የመጡ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የማዘዝ ሥልጣን አላቸው።

## የግንባታ ሕግ/ደንብ

ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያለ ማንኛውም ነገር መብቶችን፣ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን እና በዮናይትድ እስቴትስ (በአሜሪካ) ሕገ መንግሥት ሥር የሚገኙ መፍትሄዎችን፣ 1990 ዓ.ም የተላለፈውን ጉድለት ያለባቸው አሜሪካውንን የሚመለከተውን ድንጋጌ፣ በ1973 ዓ.ም የተላለፈውን መልሶ የማቋቋም ድንጋጌ አርዕስት 5 (ክፍል 504) ወይም፣ ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያለውን እፎይታ በመሻት፣ በእነዚህ ሕጎች ሥር ያለውን የመንግሥት እርምጃ ከመጠየቅዎ በፊት ከላይ የተጠቀሱት ሕጋዊ የአሰራር ቅደም ተከተሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ያለው እርምጃ እንዲወሰድ አንድ አካል ጠይቆ በሚደረገው ልክ ከላይ የተሰጡ የአሰራር ቅደም ተከተሎች ተሟጠው መከናወን ያለባቸው ካልሆነ በቀር፣ ጉዳት ያለባቸውን ልጆች መብቶች የሚጠብቁ ሌሎች የፌዴራል ህጎችን አይገድብም ወይም አይወስንም። ነገር ግን፣ በአጠቃላይ ሲታይ፣ ቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄድ በእነዚያ ሌሎች ህጎች ስር እፎይታ ለማግኘት፣ በመጀመሪያ ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ሥር ያሉ አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን (ማለትም ቅሬታን/ስሞታን በጽሁፍ ማቅረብን፣ የውሳኔ ስብሰባን፤ ገለልተኛ የማድመጥ ቅደም ተከተሎችን) መጠቀም አለብዎት።

### *ቅሬታን በጽሁፍ የማቅረብና የማድመጥ ሂደቶችን እየጠበቁ ሳሉ የልጅ ምደባ/ለልጁ ቦታ መስጠት*

ከዚህ በታች ***ጉድለት/ውስንነት ባለባቸው ልጆች ላይ የድስፕሊን እርምጃ ሲወሰድ መከተል ያለብን የአሰራር ቅደም ተከተሎች*** በሚል ርዕስ ሥር በቀረበው መንገድ ካልሀነ በስተቀር ለሌላኛው አካል ቅሬታ በጽሁፍ ከተላከ፣ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት እና በገለልተኛ አካል ለመሰማት ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ እየተጠበቀ ሳለ፣ እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ከዚህ በተለየ ሁኔታ ካልተስማማችሁ በቀር፣ ልጅዎ አሁን ባለበት/ባለችበት የትምህርት ምድብ መቆየት አለበት/አለባት። ቅሬታን/ስሞታን በጽሁፍ የማቅረብ ሂደቱ ለመነሻነት ወደ መንግሥት ትምህርት ቤት ለመግባት ማመልከቻ ማስገባትን የሚያካትት ከሆነ ልጅዎ በእርስዎ ስምምነት እንደዚህ ያሉት የአሰራር ሂደቶች በሙሉ እስኪጠናቀቁ ድረስ መደበኛ በሆነ የመንግሥት ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ መሆን አለበት/ባት። ስሞታን በጽሁፍ የማቅረብ ሂደቱ ጉድለት/ውስንነት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ሐ ሥር ከመገልገል ወደ ክፍል ለ ሥር እየተሻገረ/ች ላለ/ች ልጅ በ«ለ» ሥር ያለ አገልግሎትን እንዲያገኝ/እንድታገኝ ለመነሻ አገልግሎቶች ማመልከቻ ማስገባትን የሚያካትት ከሆነ እና ልጁ/ልጅቷ እድሜው/ዕድሜዋ ሶስት ስለሆነ በ«ሐ» ሥር ላሉ አገልግሎቶች ብቁ ስላልሆነ/ች የአከባበው የትምህርት አስተዳደር ልጁ/ልጅቷ እየተቀበለ/ች ያለውን በ«ሐ» ስር ያለውን አገልግሎት እንዲሰጥ አይጠበቅበትም። ልጅዎ ጉዳት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ስር ላለው አገልግሎት ብቁ ሆኖ/ሆና ከተገኘ/ች እና እርስዎም ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች እንዲያገኝ/እንድታገኝ ከተስማሙ፣ የሂደቱ ውጤት እየተጠበቀ ሳለ፣ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እነዚያን በግጭት ውስጥ የሌሉትን ልዩ ትምህርትንና

ተዘማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ማቅረብ አለበት (እርስዎና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የተስማማችሁባቸውን አገልግሎቶች)።

## *የሕግ ባለሙያዎች/አቃቤ ሕግ ክፍያዎች*

### አጠቃላይ

ጉደለት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር በተቀመጣው በማንኛውም ድርጊት ወይም ሂደት ውስጥ እርስዎ ካሸነፉ፣ ፍርድ ቤቱ፣ በራሱ ውሳኔ፣ እርስዎ ያወጡአቸው ወጪዎች አካል አድርጎ አሳማኝ የሆነ የህግ ባለሙያ ክፍያዎችን ሊሰጥዎት ይችላል። ጉድለት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር በመጣው በማንኛውም ድርጊት ወይም ሂደት ውስጥ ፍርድ ቤቱ፣ በራሱ ውሳኔ፣ ለሚያሸንፈው የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር፣ በአቃቤ ሕጉ መከፈል ያለበትን አሳማኝ የሆነ የአቃቤ ሕግ ክፍያዎችን ይከፍላል። ይህ የሚሆነው አቃቤ ሕጉ፡-(ሀ) ዋጋ ቢስና ምክንያታዊ ያልሆነ ወይም መሰረት የሌለው ቅሬታ ወይም ክስ ካቀረበ ነው፤ **ወይም** (ለ) ሙግቱ እርባና የሌለው፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ወይም መሰረተ ቢስ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ሙግቱን ከቀጠለ።

ጉድለት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ባለው በማንኛውም ድርጊት ወይም የፍርድ ቤት ሂደት ውስጥ እርስዎ የፍርድ ሂደቱ እንዲሰማ ከጠየቁ ወይም ኋላ ክሱ እንደ ማስፈራራት፣ አስፈላጊ ያልሆነ መዘግየትን ለመፍጠር ወይም የድርጊቱ ወይም የፍርድ ሂደቱ አለስፈላጊ በሆነ ሁኔታ ወጪ እንዲጨምር በማድረግ ለማንኛውም ላልተገባ ዓላማ ከቀረበ ፍርድ ቤቱ፣ በራሱ ውሳኔ፣ እርስዎ ወይም አቃቤ ሕጉ መክፈል የነበረባችሁን ክፍያ እንደ ተመጣጣኝ የአቃቤ ሕግ ክፍያ በማድረግ ላሸነፈው የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ይሰጣል።

### ክፍያዎችን መስጠት

ፍርድ ቤት ተመጣጣኝ የሆነ የአቃቤ ሕግ ክፍያዎችን እንደሚከተለው ይሰጣል፡-

1. ለተሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶችና ጥራቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች ድርጊቱ ወይም የፍርድ ሂደቱ በተካሄደበት ህብረተሰብ ውስጥ ባሉ ደረጃዎች ተመስርቶ መሆን አለበት። የሚሰጡ ክፍያዎች በሚሰሉበት ጊዜ ምንም ዓይነት ጉርሻ ወይም ማባዛት ጥቅም ላይ መዋል የለበትም፤
2. ጉዳዩን ለመጨረስ በጽሁፍ ከተጠየቀ በኋላ ለተፈጸሙ አገልግሎቶች ጉድለት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ላለ ለማንኛውም ድርጊት ወይም የፍርድ ቤት ሂደት በሚከተሉት ምክንያቶች ክፍያዎች የማይከፈሉ ሲሆን ተዛማጅነት ያላቸው ወጪዎችም አይወራረዱም፡-
   ሀ. ስጦታው የሚሰጠው በፌዴራል ደንቦች ውስጥ ደንብ 68 ላይ በተቀመጡ የሕዝብ አሰራር ቅደም ተከተሎች በተቀመጠው ጊዜ ወይም ልዩነቶች በሚፈቱበት ህጋዊ ሂደት ወይም በመንግስት ደረጃ በሚደረገው የክለሳ/ግምገማ ከሆነ ውሳኔ እንዲሰጥ በፍርድ ቤት የመቅረብ ሂደት ከመጀመሩ 10 ቀናት በሚበልጥ በማንኛውም ጊዜ ነው።
   ለ. ስጦታው በአስር ቀናት ውስጥ ተቀባይነት የለውም፤ **እና**
   ሐ. ፍርድ ቤቱ ወይም አስተዳደራዊ ሰሚ ባለሥልጣን በመጨረሻ ያገኙት እፎይታ ጉዳዩን ለመጨረስ ከተሰጠው የበለጠ ለእርስዎ ምቹ አይደለም።
3. እነዚህ ገደቦች ቢኖሩም እርስዎ ካሸነፉና ጉዳዩን ለመጨረስ የተሰጠውን ክፍያ አለመቀበልዎ በበቂ ሁኔታ ከተረጋገጠ የአቃቤ ሕግ ክፍያዎች ስጦታና ከዚህ ጋር ግንኙነት ያላቸው ወጪዎች ለእርስዎ ሊሰጡ ይችላሉ።
4. ስብሰባው በአስተዳደራዊ ውሳኔ ወይም ፍርድ ቤት በወሰደው እርምጃ የሚደረግ ካልሆነ በቀር ለግለሰብ ከተዘጋጀው የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ኮሚቴ ጋር ለተገናኘ ለማንኛውም ስብሰባ ክፍያ አይሰጥም። ክፍያዎች ***ሽምግልና*** ከሚለው ርዕስ ሥር ለተገለጸው የሽምግልና ሥራ አይሰጥም።

የውሳኔ ስብሰባ በሚል ርዕስ ሥር እንደተገለጸው የውሳኔ ስብሰባ አስተዳደሩ ጉዳዩን ለማሰማት ከመፈለግ ወይም በፍርድ ቤት እርምጃ የተጠራ ስብሰባ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፤ ደግሞም ለህግ አገልግሎት ክፍያ ዓላማ በአስተዳደሩ ወይም በፍርድ ቤት እርምጃ የተጠራ ስብሰባ ተደርጎ መታየትም የለበትም።

ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን ነገሮች ካገኘ ጉዳት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር የተሰጠውን የሕግ አገልግሎት ክፍያን እንደ አስፈላጊነቱ ሊቀንስ ይችላል፡-

1. እርስዎ ወይም የእርስዎ አቃቤ ሕግ ድርጊቱ በሚፈጸምበት ወይም በፍርድ ቤት የመቅረብ ተግባር በሚፈጸምበት ጊዜ የግጭቱን የመጨረሻ ውሳኔ ባልተገባ ሁኔታ ካዘገያችሁ፤
2. ለአቃቤ ሕጉ እንዲከፈል የታዘዘው ክፍያ መጠን ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ተመሳሳይ ሙያ፣ ስምና ልምድ ያላቸው አቃቤ ሕጎች ለሚሰጡአቸው ተመሳሳይ አገልግሎቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚከፈለው ክፍያ መጠን ካለፈ፤
3. የድርጊቱ ባህርይ ወይም የፍርዱ ሂደት ከግምት ውስጥ ሲገባ የፈጀው ጊዜና የተሰጡ አገልግሎቶች ከልክ በላይ ከሆኑ፤ **ወይም**
4. እርስዎን የሚወክለው አቃቤ ሕግ ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል **አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ** በሚለው ርዕስ ሥር በተገለጸው መሰረት የጥያቄ ማሳሰቢያ ላይ በቂ መረጃ ካላመስጠቱ የተነሣ። ነገር ግን የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ባልተገባ ሁኔታ የድርጊቱን የመጨረሻ ውሳኔ ወይም የሕግ ሂደት ካዘገየ ወይም ጉድለት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር የተሰጡ የአሰራር ቅደም ተከተሎች መጠበቂያዎች ከተጣሱ።

## *ጉድለት ያለባቸውን ልጆች ስንቀጣ መከተል ያለብን የአሰራር ቅደም ተከተሎች*

### የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጉዳይ ሀላፊ ሥልጣን

### የእያንዳንዱን ግለሰብ ጉዳይ እንደ ሁኔታው ለየብቻ መወሰን

የትምህርት ቤቱ የሰራተኞች ጉዳይ ሀላፊ በሚከተሉት ከቅጣት ጋር ከተገናኙ መስፈርቶች መሰረት በትምህርት ቤቱ ውስጥ የተማሪን ባህሪይ የሚመለከተውን መመሪያ ለሚጥስ ጉድለት ያለበት ልጅ ምደባን መቀየር ተገቢ መሆን አለመሆኑን በሚወስንበት ጊዜ ማንኛውንም የተለየ ሁኔታ ለየብቻ ተራ በተራ ሊያይ ይችላል።

### አጠቃላይ

ጉድለት በሌለባቸው ልጆች ላይ ደግሞ የዚህን ዓይነት እርምጃ የሚወስዱ እስከሆነ ድረስ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ጉዳይ ሀላፊ **ለተከታታይ 10 የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ** በትምህርት ቤት ከተማሪ የሚጠበቀውን ባህርይ የማያንጸባርቀውን/የማታንጸባርቀውን ጉዳት ያለበትን/ባትን ልጅ  አሁን ከተመደበበት/ከተመደበችበት በማስወጣት ወደ ሌላ ተገቢ ወደሆነ ጊዜያዊ አማራጭ ትምህርት የሚሰጥበት ቦታ ( ለልጁ/ጇ የግል ትምህርት ፕሮግራም(IEP) በሚያዘጋጀው ኮሚቴ ተወስኖ) ይወስደዋል/ይወስዳታል ወይም ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ቤት ያግደዋል/ያግዳታል።   ልጁ/ ልጅቷ ሌላ የባህርይ ግድፈት ካሳየ/ካሳየች የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጉዳይ ሀላፊ በዚያው የትምህርት ዓመት ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ ሌላ ተጨማሪ ከትምህርት ቤት የማስወጣትን ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላል። ይህ ሊሆን የሚችለው ከትምህርት ቤት ማስወጣቱ የምደባ ለውጥ የማያመጣ ከሆነ ነው (በጸባይ ግድፈት ምክንያት ከትምህርት ቤት ለተወገደ ተማሪ የምደባ ለውጥ ለሚለው ትርጉም ከዚህ በታች ይመልከቱ)። ጉዳት ያለበት/ባት ልጅ በተመሳሳይ የትምህርት ዓመት ለ10 የትምህርት ቀናት አሁን ካለበት/ችበት ምድብ ከተወገደ/ች የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ልጁ/ልጅቷ ከትምህርት ቤት በተወገደበት/ችበት በዚያ የትምህርት ዓመት በማንኛውም ቀጥለው ባሉ ቀናት ከዚህ በታች ***አገልግሎቶች*** ተብሎ በቀረበው ንዑስ ርዕስ ሥር የተጠየቁ አገልግሎቶችን ያቀርባል።

## ተጨማሪ ሥልጣን

ከአንድ ተማሪ የሚጠበቀው የባህሪይ ደንብ ጥሰት የልጁ ጉድለት/ውስንነትት መገለጫ ከሆነ (ከዚህ በታች **መገለጫዎችን መወሰን** የሚለውን ይመልከቱ) እና በጸባይ ምክንያት የሚደረገው የምደባ ለውጥ ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት የሚበልጥ ከሆነ፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ሀላፊ ጉድለት የሌለባቸውን ልጆች ለመቅጣት የሚወስዳቸውን የአሰራር ቅደም ተከተሎች በተመሳሳይ ሁኔታና ለተመሳሳይ የጊዜ ርዝማት ጉድለት ላለበት ልጅም ይተገብራል። ጉድለት ከሌለባቸው ተማሪዎች ልዩ የሚሆነው ትምህርት ቤቱ ለዚህ ልጅ ከዚህ በታች አገልግሎቶች ከሚለው ስር በተገለጸው መሰረት አገልግሎቶችን ማቅረቡ ነው። ለልጁ በግል ደረጃ የሚዘጋጅ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ኮሚቴ እነዚህን የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታን ይወስናል።

## አገልግሎቶች

በአሁኑ ወቅት ከሚማርበት/ከምትማርበት ምድብ ለተወገደው/ለተወገደችው ጉድለት ላለበት/ላለባት ልጅ መሰጠት ያለባቸው አገልግሎቶች ጊዜያዊ በሆነ አማራጭ የትምህርት ቦታ ሊሰጡ ይችላሉ። የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በትምህርት ዓመቱ አሁን ካለበት/ችበት  ምድብ ለ10 የትምህርት ቀናት ወይም ከዚያ ላነሳ ጊዜ ለተወገደ/ች ልጅ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ የሚጠበቅበት በተመሳሳይ ምክንያት ከትምህርት ቤት ለተወገደ/ች ጉድለት የሌለበት/የሌለባት ልጅ አገልግሎቶቹን የሚሰጥ ከሆነ ብቻ ነው። ጉድለት ያለበት/ያለባት እና አሁን ካለበት/ካለችበት የትምህርት ምድብ ከ10 ቀናት በላይ የተወገደ/ች ልጅ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለበት/አለባት፡-

1. በሌላ ሁኔታ ቢሆንም፣ ልጁ/ልጅቷ በአጠቃላይ የትምህርት ስርዓተ-ትምህርት መሳተፉን/መሳተፏን እንዲቀጥል/እንድትቀጥል ለማድረግ እና በልጁ/በልጅቷ በግል ደረጃ በሚዘጋጅ የትምህርት ፕሮግራም ከተቀመጡ ግቦች ላይ ለመድረስ ወደ ፊት ለመገስገስ የትምህርት አገልግሎቶችን ማግኛቱን/ቷን መቀጠል አለበት/አለባት። **እና**
2. እንደ አመቺነቱ የባህሪይ ጥሰቱ እንደገና እንዳይከሰት ለማድረግ ለተከሰቱ የባህሪይ ጥሰቶች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጁ የሚሰራ የባህሪ ዳሰሳን እና በባህሪይ ላይ ጣልቃ የመግባት አገልግሎቶችንና ማስተካከያዎችን ማግኘት አለበት/አለባት።

ጉድለት ያለበት/ያለባት ልጅ ለትምህርት ከተመደበበት/ከተመደበችበት ቦታ በዚያው ዓመት ለ10 ቀናት ከተወገደ/ች በኋላ አሁን ከትምህርት ቤት የተወገደው/ችው ለ10 ተከታታይ ቀናት ወይም ከዚያ ለሚያንስ ጊዜ ከሆነ እና ከትምህርት ቤት መወገዱ/ዷ የምደባ ለውጥ ካልሆነ (ከዚህ በታች ያለውን ትርጉም ይመልከቱ) የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ሀላፊ፣ ቢያንስ ከልጁ/ከልጅቷ መምህራን መካከል ከአንዱ/ዷ ጋር በመመካከር ልጁ/ልጅቷ በሌላ ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም፣ በአጠቃላይ የትምህርት ስርዓተ-ትምህርት ላይ መሳተፉን/መሳተፏን እንዲቀጥል/እንድትቀጥል ለማድረግና ለልጁ/ለልጅቷ በግል ደረጃ በተዘጋጀው የትምህርት ፕሮግራም ላይ የተቀመጡ ግቦችን ለመምታት ወደ ፊት ለመገስገስ የሚያስፈልጉ ተገቢ አገልግሎቶችን መጠን ይወስናል።  ከትምህርት ቤት ማስወጣቱ የምደባ ለውጥ ከሆነ (ከዚህ በታች ያለውን ትርጉም ይመልከቱ) ለልጁ/ልጅቷ በግል ደረጃ የትምህርት ፕሮግራም የሚያዘጋጀው ኮሚቴ ልጁ/ልጅቷ በአጠቃላይ የትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ላይ መሳተፉን/ፏን እንዲቀጥል/እንድትቀጥል ለማድረግና ለልጁ/ለልጅቷ በግል ደረጃ በተዘጋጀው የትምህርት ፕሮግራም ላይ የተቀመጡ ግቦችን ለመምታት ወደ ፊት ለመገስገስ የሚያስፈልጉ ተገቢ አገልግሎቶችን መጠን ይወስናል።

## መገለጫዎችን መወሰን

ጉድለት ያለበት/ያለባት ልጅ ከአንድ ተማሪ የሚጠበቀውን የባህሪይ ደንብ ከመጣሱ/ሷ የተነሣ የልጁን/የልጅቷን ምደባ ለመቀየር ውሳኔ በተደረገበት በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ (ከት/ቤት መወገዱ/ዷ ለተከታታይ 10 ቀናት ወይም ከዚያ ላነሳ ጊዜ እስከሆነ እና እርሱም የምደባ ለውጥ እስካልሆነ ድረስ) የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር፣ ወላጅና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ለልጁ/ለልጅቷ የግል የትምህርት ፕሮግራምን የሚያዘጋጅ ኮሚቴ አባላት (በወላጅና በአከባቢው የትምህርት

አስተዳደር በተወሰነው መሰረት) የልጁን/የልጅቷን በግል ደረጃ የተዘጋጀውን የትምህርት ፕሮግራም ጨምሮ በተማሪው ፋይል ውስጥ ያለውን ሁሉንም አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች፣ የመምህሩን እይታዎች እና የሚከተሉትን ነገሮች ለመወሰን በወላጆች የተሰጠውን ማንኛውንም አግባብነት ያለውን መረጃ መገምገም አለባቸው፡-

1. በጥያቄ ውስጥ ላለው ባህሪይ መንስኤው የልጁ/የልጅቷ ጉዳት ከሆነ ወይም ከጉዳቱ ጋር ቀጥተኛና ጠንካራ ግንኙነት ካለው፤ **ወይም**
2. በጥያቄ ውስጥ ያለው ባህሪይ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለልጁ/ለልጅቷ በግል ደረጃ የሚዘጋጀውን የትምህርት ፕሮግራም መተግበር ያለመቻሉ ቀጥተኛ ውጤት ከሆነ።

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር፣ ወላጅ፣ እና ለልጁ/ለልጅቷ የግል ትምህርት ፕሮግራም አዘጋጅ ኮሚቴ አግባብነት ያላቸው አባላት ከእነዚህ ሁኔታዎች አንዱም ተፈጻሚ መሆኑን ከወሰኑ፣ ባህሪዩ የልጁ/ልጅቷ ጉድለት መገለጫ መሆኑን ይወስናሉ። በጥያቄ ውስጥ ያለው ባህርይ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለልጁ/ለልጅቷ በግል ደረጃ የሚዘጋጀውን የትምህርት ፕሮግራም መተግበር ያለመቻሉ ቀጥተኛ ውጤት መሆኑን የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር፣ ወላጅ፣ እና ለልጁ/ለልጅቷ በግል ደረጃ የሚያዘጋጀውን የትምህርት ፕሮግራም የሚያዘጋጅ ኮሜቴ አግባብነት ያላቸው አባላት ከወሰኑ፣ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እነዚያን ጉድለቶች ለማከም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አለበት።

### የሚንጸባረቀው ባህሪይ የልጁ/የልጅቷ ጉድለት መገለጫ መሆኑን መወሰን

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር፣ ወላጅ፣ እና ለልጁ/ለልጅቷ የግል ትምህርት ፕሮግራም አዘጋጅ ኮሚቴ አግባብነት ያላቸው አባላት ባህሩዩ የልጁ/ልጅቷ ጉድለት መገለጫ መሆኑን ከወሰኑ (ካረጋገጡ)፣ ለልጁ/ለልጅቷ በግል ደረጃ የሚዘጋጅ የትምህርት ፕሮግራምን የሚያዘጋጅ ኮሚቴ ከሚከተሉት አንዱን ሊያደርግ ይችላል፡-

1. የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የምደባ ለውጥ ከመደረጉ በፊት የሚሰራ የባህሪይ ዳሰሳን እና የልጁን/የልጅቷን ባህሪይ ለመለወጥ የሚደረግ ጣልቃ የመግባት ዕቅድን ተግባራዊ አድርጎ ካልሆነ በቀር የሚሰራ የባህሪይ ዳሰሳን ያደርጋል፤ **ወይም**
2. በባህሪይ ላይ ጣልቃ የመግባት ዕቅድ አስቀድሞውኑ ተዘጋጅቶ ከሆነ ለተከሰተው የባህሪይ ችግር መፍትሄ ለመስጠት የባህሪይ ጣልቃ የመግባት ዕቅዱን ይገመግምና እንደ አስፈላጊነቱ ያስተካክላል።

ከዚህ በታች **ልዩ ሁኔታዎች** በሚል ንዑስ-ርዕስ ሥር የተገለጸውን ሳይጨምር፣ ወላጅና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የምደባ ለውጡ የባህሪይ ጣልቃ የመግባት ዕቅድ ማስተካከያ አካል ነው ብለው ካልተስማሙ በቀር፣ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ልጁን/ልጅቷን ወደተወገደበት/ወደተወገደችበት ምድብ መመለስ አለበት።

### ልዩ ሁኔታዎች

ባህሪይ የልጁ ጉድለት መገለጫ ቢሆንም ባይሆንም የትምህርት ቤቱ የሰራተኞች ሀላፊ በሚከተሉት ምክንያቶች ልጁን ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ እስከ 45 ቀናት ለሚደርስ ጊዜ ሊወስድ ይችላል (ለልጁ በግል ደረጃ የሚዘጋጀውን የትምህርት ፕሮግራም በሚያዘጋጅ ኮሚቴ ተወስኖ) ፡-

1. ወደ ትምህርት ቤት የጦር መሣሪያ ይዞ ከመጣ (ከዚህ በታች ያለውን ትርጉም ይመልከቱ) ወይም መሣሪያ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት አከባቢ ወይም በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሥልጣን ሥር ባለው የትምህርት ቤቱ ማህበራዊ ፕሮግራም ላይ ይዞ ከተገኘ፤
2. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት አከባቢ፣ በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሥልጣን ሥር ባለው የትምህርት ቤቱ ማህበራዊ ፕሮግራም ላይ እያወቀ ህገወጥ መድሃኒቶችን ይዞ ከተገኘ ወይም ከተጠቀመ (ትርጉሙን

ከዚህ በታች ይመልከቱ) ፣ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበትን እጽ ከሸጠ ወይም እንዲሸጥ ካግባባ (ትርጉሙን ከዚህ በታች ይመልከቱ) ፣ **ወይም**

3. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት አከባቢ ወይም በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር *ሥ*ልጣን *ሥ*ር ባለው የትምህርት ቤቱ ማህበራዊ ፕሮግራም ላይ ሳለ በሌላ ሰው ላይ ከባድ አካላዊ ጉዳት አድርሶ ከሆነ (ትርጉሙን ከዚህ በታች ይመልከቱ) ።

## ትርጉሞች

*ቁጥጥር የሚደረግበት እጽ ማለት መድሃኒት ወይም* ቁጥጥር የሚደረግበት እጽ ድንጋጌ (21 U.S.C. 812(b) መርሀ-ግብር I, II, III, IV, ወይም V ክፍል 202(b) *ሥ*ር ተለይቶ የሚታወቅ ሌላ ነገር ማለት ነው። *ሕገ ወጥ መድሃኒት* ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት እጽ ሲሆን ፈቃድ በተሰጣቸው የጤና ባለሙያዎች ቁጥጥር *ሥ*ር ሆኖ በሕጋዊ ሁኔታ የሚያዘውን ወይም ጥቅም ላይ የሚውለውን ወይም በዚያ ድንጋጌ *ሥ*ር ወይም በሌላ በማንኛውም የፌዴራል ሕግ *ሥ*ር በማንኛውም ባለሥልጣን *ሥ*ር ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ የሚያዝና ጥቅም ላይ የሚውል ነገርን አያካትትም። *ከባድ አካላዊ ጉዳት* የሚለው በአሜሪካ መንግሥት ህግ አንቀጽ 3 ንዑስ ክፍል ኤች ክፍል 1365 ርዕስ 18 *ሥ*ር ከባድ አካላዊ ጉዳት የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል። *የጦር መሣሪያ* የሚለው በአሜሪካ ህግ አንቀጽ 2 የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል ጂ ክፍል 930 ርዕስ 18 *ሥ*ር «አደገኛ መሣሪያ» የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል።

## ማስታወቂያዎች

ልጁ የተማሪ ባህሪይ ደንብን ስለጣሰ የምድብ ለውጥ የሆነው ከትምህርት ቤት የማስወጣት ውሳኔ በሚደረግበት ቀን የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለወላጆች ውሳኔውን ማሳወቅና ለወላጆቹ የአሰራር ቅደም ተከተል መጠበቂያዎችን ማሳሰቢያ (የሰነዱን ቅጂ) መስጠት አለበት።

## ከባህሪይ ጉድለት የተነሳ ከትምህርት ቤት በመወገዱ የሚደረግ የምደባ ለውጥ

ጉዳት ያለበትን ልጅ አሁን ከሚማርበት የትምህርት ምድብ ማስወጣት ከሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ **የምድብ ለውጥ** ነው፡-

1. ከትምህርት ቤት እንዲወጣ የተደረገው ለ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ከሆነ፤ ወይም
2. ልጁ በሚከተሉት ምክንያቶች ልማድ እስኪሆን ድረስ በተደጋጋሚ ከትምህርት ቤት መውጣት ገጥሞት ከሆነ፡-
   ሀ. ከትምህርት ቤት በተከታታይ የወጠባቸው ቀናት በዓመት ውስጥ ከ10 የትምህርት ቀናት ከበለጠ፣
   ለ. የልጁ ባህሪይ አስቀድሞ በተከታታይ ከትምህርት ቤት እንዲወገድ ካደረጉ ክስተቶች *ጋ*ር በመሰረቱ ተመሳሳይ ከሆነ **እና**
   ሐ. እያንዳንዱ ከትምህርት ቤት የተወገደበት የጊዜ ርዝማት፣ ልጁ ከትምህርት ቤት የተወገደበት አጠቃላይ ሰዓት እና አንዱ ከትምህርት ቤት መወገድ ለሌላኛው ያለው ቅርበት የሚመስሉ ነገሮች።

ከትምህርት ቤት የማስወገድ ሞዴል በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እንደ ጉዳዩ ሁኔታ የተወሰነ የምደባ ለውጥን የሚያካትት ሲሆን ጥያቄ ከተነሳበት ልዩነት በሚፈታበት ሕጋዊ ሂደት ወይም በሕግ አካል ውሳኔ የሚከለስ ይሆናል።

## አከባቢን/ ቦታን መወሰን

በግል ደረጃ የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ኮሚቴ **የምደባ ለውጥ** የሆኑ ከትምህርት ቤት ማስወጣትንና ከላይ **ተጨማሪ ሥልጣን** እና **ልዩ ሁኔታዎች** በሚሉ ርዕሶች *ሥ*ር የቀረቡ ከትምህርት ቤት ማስወጣትን በተመለከተ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታን መወሰን አለበት።

## ተማጽኖ

### አጠቃላይ

ጉድለት ያለበት ልጅ ወላጅ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ካልተስማማ ጉድለት ባለበት የተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት የሚፈታበት ህጋዊ ሂደት እንዲካሄድ አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል (ከላይ ይመልከቱ)፡-

1. በዚህ የድስፕሊን እርምጃ በሚያስቀምጣቸው ነገሮች ሥር ምደባን በተመለከተ ባለው በማንኛውም ውሳኔ ላይ፤ **ወይም**
2. ከላይ በተገለጸው መሰረት መገለጫዎችን መወሰን በሚለው ላይ።

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ልጁ የተሰጠውን ምደባ ጠብቆ ማስቀጠል ለልጁም ሆነ ለሌሎች የጎላ ጉዳት ያስከትላል ብሎ ካመነ ጉድለት ባለበት የተማሪ ወላጅና በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት የሚፈታበት ህጋዊ ሂደት እንዲካሄድ አቤቱታን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል (ከላይ ይመልከቱ) ።

### ጉዳዩን የሚከታተል ሀላፊ ሥልጣን

***ገለልተኛ የሆነ ጉዳዩን ተከታታይ ሀላፊ*** በሚለው ሥር የተገለጹ መስፈርቶችን የሚያሟለው ጉዳዩን የሚከታተል ሀላፊ ጉዳዩን ሰምቶ ውሳኔ መስጠት አለበት። ጉዳዩን የሚከታተለው ሀላፊ፡-

1. ጉዳዩን የሚከታተለው ሀላፊ ልጁን ከትምህርት ቤት ማስወገድ **የትምህርት ቤት ሰራተኞች ሀላፊ ሥልጣን** በሚለው ሥር የተገለጹ መስፈርቶችን መጣስ ነው ብሎ ከወሰነ ወይም የልጁ ባህርይ የጉዳቱ መገለጫ ከሆነ ጉዳተኛ የሆነውን ልጅ እንዲወጣ ወደተደረገበት ቦታ ይመልሰዋል፤ **ወይም**
2. ጉዳዩን የሚከታተለው ሀላፊ ልጁ አሁን ባለበት ምድብ እንዲቆይ ማድረግ ለልጁ ወይም ለሌሎች ጉልህ የሆነ ጉዳት ያደርሳል ብሎ ከወሰነ ልጁ ከ45 የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ተገቢ በሆነ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ ላይ እንዲመደብ ያዛል።

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ልጁን አስቀድሞ ተመድቦ ወደነበረበት ቦታ መመለስ ለልጁ ለራሱ ወይም ለሌሎች ጉልህ የሆነ ጉዳት ያስከትላል ብሎ ካመነ እነዚህ ጉዳዩን የመከታተል ቅደም ተከተሎች ሊደገሙ ይችላሉ። ወላጅ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጉዳዩ እንዲታይ አቤቱታን በጽሁፍ ሲያቀርብ በሚከተሉት ምክንያቶች ካልሆነ በቀር ***አቤቱታን የመስማት ቅደም ተከተሎች፣ በጽሁፍ የቀረቡ አቤቱታዎችን መስማት*** እና ***የውሳኔዎች ይግባኝ፣ ገለልተኛ ግምገማ/ክለሳ*** በሚሉ ርዕሶች ሥር የተገለጹ መስፈርቶችን በሚያሟላ መልኩ ጉዳዩ መታየት አለበት፡-

1. የኔቫዳ የትምህርት ክፍል ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጉዳዩ እንዲሰማ ጥያቄ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ20 ቀናት ውስጥ በአፋጣኝ ጉዳዩን የመፍታት ሂደት እንዲጀመር ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት። ጉዳዩ ከታየ/ከተሰማ በኋላ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ከውሳኔ ላይ መደረስ አለበት።
2. ወላጆችና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ስብሰባውን ለመተው ወይም ሽምግልናን ለመጠቀም በጽሁፍ ካልተስማሙ በቀር፣ ጉዳዩ እንዲታይ የጽሁፍ አቤቱታ በቀረበ ሰባት ቀናት ውስጥ ውሳኔ የሚሰጥበት ስብሰባ መካሄድ አለበት። አቤቱታ በጽሁፍ በቀረበበት በ15 ቀናት ውስጥ ሁለቱንም ወገኖች በሚያረካ ሁኔታ ጉዳዩ እስኪፈታ ድረስ ጉዳዩን ማየት/መስማት ይቀጥላል።
3. መንግሥት ሌሎች ጉዳዮች የሚፈቱበትን ሕጋዊ ሂደት ካዘጋጀው በበለጠ ሁኔታ ጉዳዮች በፍጥነት የሚፈቱበትን ሕጋዊ ሂደት ሊመሰርት ይችላል፤ ነገር ግን የጊዜ ገደቦቹ ካልሆኑ በስተቀር ያለው ችግር የሚፈታበትን ህጋዊ ሂደት በተመለከተ እነዚያ ሕጎች በሰነዱ ውስጥ ካሉ ህጎች ጋር ተመሳሳይ መሆን አለባቸው።

አንድ አካል በሌሎች ልዩነቶች በሚፈቱባቸው ሕጋዊ ሂደቶች ላይ ይግባኝ እንደሚጠይቅ ሁሉ ውሳኔው በአፋጣኝ

እንዲታይለት ይግባኝ መጠየቅ ይችላል (ከላይ ይግባኝ የሚለውን ይመልከቱ) ፡፡

### ምደባ በይግባኝ ጊዜ

ከላይ በተገለጸው መሰረት ወላጅ ወይም የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ከድስፕሊን ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን በተመለከተ አቤቱታን በጽሁፍ ሲያቀርብ ልጁ (ወላጅና የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በቀር) ጉዳዩን የሚመለከተውን ሀላፊ ውሳኔ እየተጠባበቀ ወይም የትምህርት **ቤት ሀላፊ ስልጣን** በሚለው ርዕስ ሥር በተሰጠውና በተገለጸው መሰረት የማስወጣት ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ መቆየት አለበት፡፡

### ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ለማግኘት ገና ብቁ ላልሆኑ ልጆች የሚደረጉ ጥበቃዎች አጠቃላይ

አንድ ልጅ ለልዩ ትምህርትና ተዛማጅነት ላላቸው አገልግሎቶች ብቁ ነው ተብሎ ካልተወሰነ እና የተማሪን የባህሪይ ደንብ ጥሶ ከተገኘ፣ ነገር ግን የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የድስፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ ስላደረገው ባህሪይና ልጁ ጉድለት የነበረበት እንደነበረ አስቀድሞ እውቀት (ከዚህ በታች እንደተወሰነው) እስከነበረው ድረስ ልጁ በዚህ ማሳሰቢያ ውስጥ ከተገለጹ ጥበቃዎች ውስጥ የትኛውንም ቢሆን ለማግኘት መጠየቅ ይችላል፡፡

### ለድስፕሊን ጉዳዮች የእውቀት መሰረት

በሚከተሉት ምክንያቶች የድስፕሊን እርምጃ እንዲከሰት ያደረገው ባህሪይ ከመከሰቱ በፊት ልጁ ጉድለት ያለበት ልጅ ስለመሆኑ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር እውቀት እንዳለው መታሰብ አለበት፡-

1. የልጁ ወላጅ ጉዳዩን ለሚከታተለው ወይም ተገቢ ለሆነ የትምህርት ወኪል የአስተዳደር ሀላፊ ወይም ለልጁ መምህር ልጁ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅነት ያላቸው አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት ያለውን ሀሳብ በጽሁፍ ስለገለጸ.
2. ጉድለት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ለ ሥር ላለው ልዩ ትምህርትና ተዛማጅነት ላላቸው አገልግሎቶች ብቁ ስለመሆኑ ግምገማ እንዲደረግ ስለጠየቀ፤ **ወይም**
3. የልጁ ወላጅ ወይም ሌላ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሀላፊ ልጁ እያሳየ ስላለው ባህሪይ ስላለው ስጋት ልዩ ትምህርትን ለሚከታተለው የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሥራ መሪ ወይም ለሌላ የለአከባቢው የትምህት አስተዳደር ተቆጣጣሪ ግለሰብ በቀጥታ ስለነገረ፡፡

### ይህ የማያካትታቸው ነገሮች

በሚከተሉት ምክንያቶች የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የዚህ ዓይነት እውቀት እንዲኖረው አይጠበቅበትም፡-

1. የልጁ ወላጅ ለልጁ ግምገማ እንዲደረግ ስላልፈቀደ ወይም ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች እንዲሰጡት ስላልፈቀደ፤ **ወይም**
2. ልጁ ግምገማ ተደርጎለት ጉድለት ያለባቸውን ልጆች በሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር ባለው መሰረት ልጁ ጉድለት እንደሌለበት ስለተወሰነ፡፡

### የእውቀት መሰረት ከሌለ ሥራ ላይ የሚውሉ ሁኔታዎች

በልጁ ላይ የድስፕሊን እርምጃ ከመወሰዱ በፊት የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር **ለድስፕሊን ጉዳዮች የእውቀት መሰረት እና ይህ የማያካትታቸው ነገሮች** በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር ከላይ እንደተገለጸው ልጁ ጉድለት ያለበት ልጅ ስለመሆኑ እውቀት እስከሌለው ድረስ በልጁ ላይ የሚወሰዱ የድስፕሊን እርምጃዎች ከዚህ ጥፋት ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጥፋት ላይ በተገኙ ጉድለት የሌለባቸው ልጆች ላይ የሚወሰዱ የድስፕሊን እርምጃዎች ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን ልጁ በድስፕሊን እርምጃ ላይ በነበረበት ወቅት ግምገማ እንዲደረግ ጥያቄ ቀርቦ ከሆነ ግምገማው በአፋጣኝ መደረግ አለበት፡፡ ግምገማው

እስኪጠናቀቅ ድረስ ከትምህርት ቤት ለተወሰነ ጊዜ ማገድን ወይም ከትምህርት አገልግሎቶች ማስወጣትን ማካተት በሚችሉ በትምህርት ቤት ባለሥልጣናት በተወሰነ የትምህርት ምደባ ውስጥ ይቆያል። በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር የተደረገውን ግምገማና በወላጆች የተሰጠውን መረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ልጁ ጉድለት ያለበት ልጅ መሆኑ ከተወሰነ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጉድለት ያለባቸውን ግለሰቦች በሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ ሥር በተመለከተው መሰረት፣ ከላይ የተገለጹ የድስፕሊን መስፈርቶችን ጨምሮ ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት አለበት።

### ወደ ሕግ አስፈጻሚዎችና የፍትህ አካላት መምራትና በሕግ አስፈጻሚዎችና ባለሥልጣናት የሚወሰድ እርምጃ

ጉድለት ያለባቸውን ግለሰቦች የሚመለከት የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ፡-

1. ጉድለት ባለበት ልጅ የሚፈጸም ወንጀልን ለሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ሪፖርት እንዳያደርግ ወኪሉን ይከለክላል፤ **ወይም**
2. የመንግሥት ሕግ አስፈጻሚዎችና የፍትህ አካላት ባለሥልጣናት ጉድለት ባለበት ልጅ ለተፈጸሙ ወንጀሎች የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ሕግ እንዳይተገብሩ ይከለክላል።

### የተመዘገቡ መረጃዎችን ማስተላለፍ

የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጉድለት ያለበት ልጅ ስለ ፈጸመው ወንጀል መረጃን ከሰጠ የአከባቢው የትምህህርት አስተዳደር፡-

1. ለልጁ የተሰጡ የልዩ ትምህርትና የድስፕሊን እርምጃ መረጃዎች ቅጂዎች እንዲታዩ ወኪሉ የወንጀሉን መረጃ ለሚያስተላልፍላቸው ባለሥልጣናት መተላለፋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፣ እና
2. የቤተሰብ የትምህርት መብቶችንና ለብቻቸው የመሆን መብትን የሚተገብሩ ደንቦች እስከፈቀዱ ድረስ ብቻ የልጁን ልዩ ትምህርትና የድስፕሊን መረጃዎችን ቅጂ ማስተላለፍ ይችላሉ።

## *ወላጆች ልጆችን በአንድ ወገን ውሳኔ ብቻ በመንግሥት ወጪ በግል ትምህርት ቤቶች እንዲመደቡ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች*

### አጠቃላይ

ጉድለት ያለባቸውን ግለሰቦች የሚመለከተው የትምህርት ድንጋጌ ክፍል ለ መሰረት የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለሁሉ ተደራሽ የሆነ ነጻና ተገቢ ትምህርት አቅርቦ ሳለ እርስዎ ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት ለማስገባት ከመረጡ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ጉድለት ላለበት ልጅዎ የሚሰጡ ልዩ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ጨምሮ የትምህርት ወጪን እንዲከፍል አይጠየቅም። ነገር ግን የግል ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በ300.144 አማካይነት በ34 CFR §§300.131 ሥር በወላጆቻቸው የግል ትምህርት ቤት እንዲገቡ የተደረጉ ልጆችን በተመለከተ ፍላጎቶቻቸው በ«ለ» ሥር በተመለሰላቸው ሕዝብ ውስጥ ልጅዎን ማካተት አለበት።

### በግል ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ/ለማስመደብ ክፍያ

ልጅዎ ከዚህ በፊት በአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ሥልጣን ሥር የተለየ ትምህርትንና ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች ተቀብሎ ከሆነ እና እርስዎ ያለ አከባቢው የትምህርት አስተዳደር ስምምነት ወይም ወደ ሌላ ትምህርት ቤት እንዲተላለፍ ሳይፈቅድ ልጅዎን ወደ ግል ትምህርት ቤት፣ የአንደኛ ደረጃ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ለማስገባት ከመረጡ ፍርድ ቤት ወይም ጉዳዩን የሚከታተል ባለሥልጣን ወኪሉ ለሁሉ ተደራሽ መሆን ያለበትን ነጻና ተገቢ ትምህርት (FAPE) ከምዝገባው በፊት በጊዜ ለልጅዎ አለማቅረቡን ካረጋገጠ እና በግል ትምህርት ቤት ማስመዝገቡ ተገቢ መሆኑን ካረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ወይም ጉዳዩን ሳሚ ባለሥልጣን ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት ለማስገባት ያወጡትን ወጪ ወኪሉ እንዲከፍል

ሊጠይቅ ይችላል። የልጅዎ ምደባ ለኔቫዳ የትምህርት ክፍልና ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ክፍል የሚሰራውን የመንግሥትን መስፈርቶች ባያሟላም ጉዳዩን የሚከታተል ባለሥልጣን ወይም ፍርድ ቤት ምደው ትክክል ሆኖ ሊያገኝ ይችላል።

### የወጣውን ወጪ በመተካት/በማወራረድ ላይ ያለ ውስንነት

ከላይ ባለው አንቀጽ ላይ የተገለጸው የወጣውን ወጪ የመተካት/የማወራረድ ተግባር በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቀነስ ወይም ሊካድ ይችላል፡-

1. (ሀ) ልጅዎን ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት በተካፈሉት እጅግ ቅርብ ጊዜ ግለሰብን ታሳቢ በማድረግ በተዘጋጀው የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ ላይ ለዚህ ኮሚቴ የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ለሁሉም ተደራሽ መሆን ያለበትን ነጻና ተገቢ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም (FAPE) ለማቅረብ ያቀረበውን ሀሳብ አለመቀበልዎንና ልጅዎን በመንግሥት ወጪ በግል ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ የገፋፊዎት ነገር ምን እንደሆነ ምክንያትዎን ካልነገሩ፤ ወይም
   (ለ) ልጅዎን ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት ቢያንስ 10 የስራ ቀናት (በሥራ ቀን የሚውለውን ማንኛውንም በዓል በመጨመር) ቀደም ብለው ስለዚህ መረጃ ለአከባቢው የትምህርት አስተዳደር በጽሁፍ ማሳሰቢያ ካልሰጡ፤
2. ልጅዎን ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት የአከባቢው የትምህርት አስተዳደር ልጅዎን ለመገምገም ስለማሰቡ (ተገቢና ምክንያታዊ ስለሆነው የግምገማ ዓለማ የሚገልጽ አረፍተ ነገርን ጨምሮ) የጽሁፍ ማሳሰቢያ ሰጥቶዎት ከሆነ፣ ግን እርስዎ ልጅዎን ለግምገማ ባለማቅረብዎ፤ ወይም
3. እርስዎ የወሰዱአቸው እርምጃዎች ምክንያታዊ (አሳማኝ) አለመሆናቸውን ፍርድ ቤቱ ካገኘ።

ነገር ግን የወጣውን ወጪ ማወራረድ/መተካት፡-

1. በሚከተሉት ምክንያቶች ማሳሰቢያ ካለመሰጣቱ የተነሳ መቀነስ ወይም መካድ የለበትም፡- (ሀ) ማሳሰቢያ እንዳይሰጡ ትምህርት ቤቱ ከከለከለዎት፤ (ለ) ከላይ የተገለጸውን ማሳሰቢያ የመስጠት ሀላፊነት እንዳለብዎ የሚገልጽ ማሳሰቢያ ስላልተሰጠዎ፤ ወይም (ሐ) ከላይ ከተቀመጡ መስፈርቶች ጋር መስማማት ለልጅዎ አካላዊ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል፤ **እና**
2. በሚከተሉት ምክንያቶች ወላጅ የሚፈለግበትን ማሳሰቢያ ካለመስጠቱ የተነሣ በፍርድ ቤቱ ወይም በሰሚ ባለሥልጣን ውሳኔ ሊቀነስ ወይም ሊካድ አይችልም፡- (ሀ) ወላጁ የተማረ ሰው ካልሆነ ወይም በእንግሊዝኛ መጻፍ ስለማይችል፤ ወይም (ለ) ከላይ ከተጠቀሰው መስፈርት ጋር መስማማት ለልጁ ከባድ የሆነ የስሜት ጉዳት ስለሚያስከትልበት።